(በብሔረሰብ ላይ የተመሠረቱ)

ጽንፈኛ አመለካከቶች

ኢትዮጵያን እንዳያወድሙብን ዘብ እንቁም

ከደስታ ቢተው

ካለፈው የቀጠለ

በኢትዮጵያ ውስጥና ውጭ በተለይ የዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎች የነበሩት ሀገር ወዳድና ዲሞክራሲያዊ ዝንባሌ የነበራቸው ዜጎቿ ያገራቸውን ኋላቀርነት ለማስወገድ ፈጣንና የተሻለ (ይበልጥ የማህበራዊና ፍትሃ መሠረት) ሆኖ የታያቸው በሶሻሊዝም መመሪያነት ተደራጅቶ፥ የሶሻሊስት ኃይሉንን ድጋፍና ትብብርም በማግኘት የነበረውን ፊውዳላዊ ሥርዓት በትግል ጥሎ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ማካሄድ ነበር። ከቀዳሚው ትውልድ መህል ሌላው ተደራጅቶና ለዲሞክራሲ ታግሎ ፊር በመቅደድ መንገድ አላላያቸውም። ስለመደራጀት ከውጭው ዓለም እንቅስቃሴዎች ተመክሮ በማጥናትና በማመሳከር ላገራችን ሁኔታ ይጠጋጋል የሚሉትን በመውሰድ ለመሥራት መሞከር ነበረባቸው። በቅን ዓላማ ተነሳስተው በሶሻሊስት (Marxist-Leninist) ርዕዮተ ዓለም መመሪያነት ፀረፊውዳል፥ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ትግል በሚያካሂዱበት ሂደት በእርግጥም አንዳንድ ስህተቶችን ፈጽመዋል። ታዲያ እኮ ጎበዝ የማይሳሳት በእርግጥም የማይሠራ ብቻ ነው! ከላይ እንደገለጽሁት በወቅቱ በዓለም ውስጥ ከፍተኛ ተቀባይነት እያገኘና እየተስፋፋም በመምጣት ላይ የነበረውን ርዕዮተዓለም ያ ወጣትና ተማሪ ትውልድ መቀበሉን በኋላ ለተከተሉ ችግሮች ሁሉ መንስዔና ምክንያት ለማድረግ መሞከር ግን ሰበብ መሻት ነው። ህቁን ብንመለከት ዓለም እኮ በሁለት ርዕዮተ ዓለማዊና ፖለቲካዊ ጎራዎች ተከፍላ እየተናወጠች ነው አስከትርብ ጊዜ ድረስ የቆየችው።

በዚያ ጊዜ የኢትዮጵያ ወጣቶች አውሮፓውያንን በጥርጣሬ ዓይን ነበር የምናያቸው:- በፋሽስት ጣሊያን መወረራችንን፥ ሌሎችም የአውሮፓ መንግሥቶች የዚያ ተባባሪዎች መሆናቸውን፥ እንደፈረንሳይ ያሉት መሣሪያ በጅቡቲ በኩል እንዳናገኝ ያደረጉብንን ተንኮል፥ ጣሊያን ከጀርመንና ጃፓን ጋር ስላበረች ጣሊያንን ወደመወረሻ የተጣላት እንግሊዝም ጣሊያንና ግብረአበሮቿን ለማቸነፍ ኋላ ከአርበኞቻችን ጋር ብትተባበርም ቆይታ ሀገራችንን ለሞዝሊትኑት (ፐሮቴክቶራት) ቃጥታ መጣሯን፥ በሶማሊያ በኩል የዘላለም ችግር የተከለችብንም እንግሊዝ መሆኗን፥ መላ አፍሪካን ተከፋፍለው ቅኝ ግዛት ማድረጋቸውን፥ ብለ-ም ሕዝቦችን በመፍጠፍጠፍ ብዙ ግፍ መፈጸማቸውን፥ ዘረኛ የደቡብ አፍሪካና የሮዴዢያ መንግሥታት እየደገፉ እንደነበሩ ... ወዘተ ከትምህርትም፥ ከውይይትም፥ ... ከሞላ ጎደል እናውቅ ነበር። አሜሪካ ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚያደርገው ...ወዘተ በወቅቱ በበርካታ የኢትዮጵያ ወጣቶች አይወደድም ነበር። የፓትሪስ ሉሙምባ በዚያ ሁኔታ መሞትም የፓን-አፍሪካዊ ስሜት የነበረውን ክፍል በጠቃላይ የምዕራብ ጥርጣሬያችን አጠናካሪ ነበር። ምዕራብን ከነርዕዮተ ዓለሙ (Capitalism) ጋር ለመጠራጠርና ለመጥላት ያኔ ወጣቱ ብዙ ምክንያት ነበሩት። የአማራጩ ርዕዮተ ዓለም (ሶሻሊዝም) ስህበት ባልተጠናከረበት ወቅት ካደጉትና ከተማሩት የቀዳሚ ትውልዶች አባላት ለየት ባለ ዓለማዊ፥ አህጉራዊና ሀገራዊ ሁኔታ ውስጥ ነበርና።

አፍቃሬ ፊውዳሉና ያሁኑ አክራሪ ብሔርተኛነትን አንጋቢ ክፍል ያንን የዲሞክራሲያዊ አብዮት ለማካሄድ የተነሣ ትውልድ፥ በተለይም በደርግ ጭፍጨፋ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበት፥ በብዙ ፀረ-ደርግ ጦርነቶችና ትግሎች ከባድ መስዋትነት ከፍሎ፥ ከጠባብ ብሔርተኞች በተሠነዘረበት ከፍተኛ ወረራና ጦርነት ተጉድቶ፥ አሁንም በአልበገሬነት በሀገራዊ ትግሉ ውስጥ ቀዳሚነትን ይዞ አቅጣጫ እየሰጠ ጉልኅ ሚና እየተጫወተ ያለውን ክፍል አይችልም እንጂ ለማጥፋት፥ በበቀል ስሜት ተነሳስቶ የሌላ ፀረ-ኢትዮጵያ ባዕድ ኃይል ተቀጣሪና ውስጣዊ አርበኛ ሆኖ የጭቃ ጅራፉን እያሳረፈበት ነው። አሁን ባለን ብስለትና የማገናዘብ ችሎታ መሠረት ለሀገራዊ ትግሉ ይበጅ ዘንድ ልዩነቶችን ላለማስፋት ካለመፈለግ ... የምናሳየውን ትእግሥት ተረድቶ ሊታቀብ አልቻለም። "ግዛኝ ብለው ሊሸጠኝ አስማማኝ" ሆነብን። በአፍላነት ዘመኑ የትውልድ ኃላፊነቱን ላይወጣ ቀርቶ አሁን በአውር ድንብር የኋሊት ይጭራል።

አክራሪ ብሔርተኛነትን የሚያቀነቅን፥ በይዘቱም አፍቃሬ ፊውዳል የሆነ፥ ከጠባብ ብሔርተኞች ባልተናነሰ መንገድ የኢትዮጵያን ሕዝቦች በዕኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነት እየጉዳ ያለ ክፍል እያውገረገረ ከሚያቀርባቸው ክሶች፥ ወቀሳዎች፥ ማጥላያዎች .... ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፤ - ቃል በቃል በመውሰድ ላይሆን ሐሳቦቹ ሲጠቃለሉ፤

1 ያ ኢትዮጵያዊ ወጣት ትውልድ ሶሻሊዝምን ወደ ሀገራችን ባያስገባብን ኖሮ ይህ ሁሉ መዓት ባል ወረደብን ነበር! አሮጌው ሥርዓትም ባልፈረሰብን ነበር! ብሎ መፀፀት÷ እናም ያን ትውልድ ተጠ ያቂና የበቀል መወጫ ለማድረግ መነሣት፤

2 ኢትዮጵያዊ ሶሻሊስት ክፍል ባያነሳው ባይቀበለው ኖሮ የብሔር ጥያቄ ባልተነሳም÷ የብሔር እንቅስ ቃሴም ባልተጠናከረ÷ .... ብሎ ከህቅ የራቀ መሠረተ ቢስ ክስ መሠንዘር፤

3 ሶሻሊዝምን መቸም ጊዜ ቢሆን ካፋቸው ያወጡት ና እምነቴ ያሉ ሁሉ ልዩነት የሌላቸው ጠላቶች ናቸው:: ደርግንም በተወሰነ ጊዜና ሁኔታ ተባብረ ውት የሠሩትም÷ ተቃውመውት የታገሉትንም÷ ጠ/ብሔርተኛ ቡድኖችንም÷ እነሱን እየተፋለሙ ያሉትን ሀገራዊ ኃይሎችንም... ደርቦ ለመምታት ከግራው ንቅናቄ ምንም ጥሩ አልተገኘም ብሎ ለማሳመን መሞከር÷ የፖለቲካ አቋም ልዩነቶችን አይቶ ለመቀበል አለመፈለግ÷ አሁንም የርዕዮተ ዓለምና የፖለቲካ ልዩነቶች ለማስተናገድ ዝግጁነ ትና ብቃት ማጣት፤

4 ጠባብ ብሔርተኛ ቡድኖች ተጠናክረው የሚታዩ ባቸው ብሔረሰቦች ተወላጅን÷ ከጠባቦች ተለይተ ው በኢትዮጵያዊነትና ባንድነት አምነው÷ ለዚሁ ዓላማ በኅ/ ብሔር ኃይሎች ውስጥና አብረው የ ሚሠሩትን እንደሰላይ ሠርጐ ገቦች በማስቆጠር ሀገራዊ ሚና እንዳይኖራቸው መገርገር:: ሌላው ቀርቶ በኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል ታሪክ ውስጥ እንደ የፖለቲካ እምነታቸው በተማሪው እንቅስቃ ሴ ውስጥና በኅብረ ብሔር የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ የታገሉትን በተለይ ጠባብ ቡድኖች ለጊዜ ው ከተጠናከሩባቸው ብሔረሰቦች የተወለዱትን 'ያኔም የሠርጐ ገብነትና የመሠሪነት ሚና ይጫ ወቱ ነበር" ብሎ መክሰስ÷ ትክክለኛውን የኢትዮ ጵያዊነት ታሪካቸውን መካድ

5 የተወሰኑ ብሔረሰቦችን ይበልጥ ኢትዮጵያዊ ማድ ረግ÷ ከእነዚህ ብሔረሰቦች የተወለዱ÷ የግራውን ርዕዮተ ዓለም አምነው ያቀነቀኑትን÷ በኅብረ ብ ሔር የተማሪና የሙያ ማኅበሮች ወይም የፖለቲ ካ ድርጅቶች ውስጥ የታገሉትን የዚያ ትውልድ አባላት በሌሎች ተጠርጣሪ በሆኑት ብሔረሰቦች ተወላጆች "የተታለሉ"÷ "የተነዱ"÷ "በየዋኅነት መሣሪያ የተደረጉ"÷ ... ብሎ ማቅረብ:: በነዚህ አክራሪ ብሔረተኞች እምነት "መሠሪነት"÷ "አ ታላይነት"÷ "ተንኩል"÷ "ብልጠት .... ወዘተ ለእነዚያው ኢትዮጵያዊነታቸው ለሚጠረጠረው ብሔረሰቦች ተወላጆች የተሰጡ ባህሪያት ሲሆኑ ከሌላው ወገን የሚወለዱትም አምነው በራሳቸው ምርጫ ውሳኔ በሚንዘበት ሁኔታ ስህተት መፈ ጸም የማይፈቅድላቸው ተነጂዎች ናቸው!

አክራሪ ብሔረተኞች ወደፊት ከማየት ፈንታ ያለፈውን በመናፈቅ ይባዝናሉ:: "ያ የትናንቱ ሥርዓት በነዚያ ያልተባረኩ÷ በሌሎች የተነዱ÷ ... ልጆቻችን ምስቅልቅሉ ባይወጣ ኖሮ ... " የሚለው ፀፀት እዛራው ችግር ላይ እንዳያተኩሩ÷ የወደፊቱንም አርቀው እንዳያዩ ጋርዷቸዋል:: ከኢትዮጵያውያን መጥፎና ጎጂ ባህሪዎች አንዱ በሆነው በበቀል ስሜት እየተነዱ በቀድሞው ፊውዳል ሥርዓት መውደቅ ተጠያቂ የሚያደርጉትን ትውልድ ማውገዝ÷ ማሳጣት÷ ከዚህም በላይ ክባዕዳን ጋርም እየተባበሩ ጭምር በዚያ ትውልድ ላይ በደርግና በጠባቦች ከደረሰበት ጉዳትና ዕልቂት ተርፎ አሁንም በሀገራዊ ትግል እየተሳተፈ ካለው ክፍል ላይ መረባረብ ቀጥለዋል:: ይወቁትም አይወቁት ይህ ተግባራቸው እያገዘ ያለው ኢትዮጵያን እያሽመደመዷት ያሉትን ጠባቦች ነው:: እናም አክራሪዎችም የአጭር ጊዜ ፖለቲካ ግብ ለመምታት ብለው የተያያዙት የሽሚያ ፖለቲካ በሕዝባችን ህላዌና አንድነት ላይ የረጅም ጊዜ ጉዳት እንደሚያከለብት አልተገነዘቡም:- "በአንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንዲባል::

የአጭር ጊዜ ግባቸው "ምናልባትም ሥልጣን የጨበጡትን ጠባብ ብሔርተኞች ታግሎ ማቸነፍ የሚቻለው በአክራሪ ብሔርተኛ ዓላማ÷ በአንድ ጠንካራ ብሔርተኛ ድርጅት ውስጥ በተለይ የአንዱን ብሔረሰብ ተወላጆች ለማሰባሰብ ሲቻል ብቻ ነው" ብለው ይህን የሚመኙትን ብሔርተኛ ድርጅት መፍጠር ነው:: ከማንኛውም ብ/ሰብ ተወላጆች መካከል÷ በአንድ ብሔረሰብ ድርጅት መሰባሰብ ተገቢ ነው ብለው የሚያምኑትንና የሚፈልጉትን የመሰብሰብ÷ የመደራጀት መብታቸውን እናውቃለን፤ እናከብራለን:: በፊትም የሌሎች ብሔረሰብ ተወላጆች በብሔር ሲደራጁ መብታቸውን አውቀናል:: ግን ብሔርተኞችን ያኔም የነገርናቸው አሁንም የምንነግራቸው በአንድ ብሔረሰብ ብሔርተኛነት መሠረት ተደራጅቶ ኅብረብሔራዊት ኢትዮጵያን በፍጹም ማቆም እንደማይቻል ነው:: አክራሪዎችም ሆኑ ጠባቦች ሕዘቧን ከፋፍለው ከማጋጨት÷ አንድነቱን የበለጠ አደጋ ላይ ከመጣል በስተቀር ሰላም÷ ዴሞክራሲና ዕድገት እንደማያስገኙ ነበር፤ ነውም:: ይህን ደግሚ እመለስበታለሁ::

ጠባብ ብሔርተኞች ፊትም ሆነ ዛሬ በተለያዩ ድርጅቶቻቸው አማካኝነት የሚፈፅሩት ኢትዮጵያ ፌርሳ ተመልሳም እንዳታንሠራራ ማሽመድመድ ስለሆነ ጠንካራ የኢትዮጵያዊነት መከሠቻ የሆኑትን÷ የቀጣይነት መሠረቷን - ኅብረ ብሔር ነክ - የፖለቲካ ድርጅቶች÷ የሙያ ማኅበሮች÷ መንግሥታዊና ማኅበራዊ ተቋሞች

መፈራረስ ያመጣበት ስለሆነ፥ በስልትና በሰቅድ በጅምላም ሆነ ተራ በተራ የቻሉትን ያህል አፍርሰዋል። እስካሁን ያልደረሱባቸውንም እየተረባረቡባቸው ነው። እናም እንደጎብሔር ሀገር ለማዳን የምንፈልጋት ሁሉ ዓላማቸውን ለማራመድ የሚያወጡትን ፖሊሲና ተግባራቸውን በይፋ ባለን ኃይል ሁሉ እየተቃወምንና እየታገልናቸው ነን። ወደፊትም ትግሉ ተጠናቅሮ መቀጠል አለበት።

ከላይ ያልኩት እንዳለ ሆኖ አሁን ሀገራዊ የሆነውን የአንድነት ትግል ፈር ሊያስት እየቃጣ ያለውና የአንድነት ኃይሎችንም ኃይልና ጎብረት በመበታተን ጠባብ ብሔረተኞችንም አስደስቶ ጮቤ ሊያስመታ የሚችለው የፖለቲካ አዝማሚያ ለኢትዮጵያ አንድነት ቆመናል በሚሉት አክራሪ ብሔረተኞች አማካኝነት በጎብረ ብሔራዊቷ ኢትዮጵያ ሀሳዊ ላይ ምናልባትም ካለማገናዘብ የተቃጣው አደጋ ነው። የጎበረ ብሔራዊቷ ኢትዮጵያ ሀሳዌ ደግሞ ይህንኑ ይዘቷን ተንከባክበው በመጠበቅ ቆመው በሚታገሉት የፖለቲካ ኃይል ተቋሞች ... ሀሳዌ አማካኝነት ነው የሚገለጠው።

አወቁትም አላወቁት አክራሪ ብሔርተኞች በጎብረ ብሔር ድርጅቶች ላይ የጀመሩት ዘመቻ እየጐዳና እየቦረቦረ ያለው ጎብረ ብሔራዊነትን፥ ከዚያ ተለይቶ የማይታየውን በ84ቱም ኢትዮጵያዊ ብሔረሰቦች እኩልነትና ወንድማማችነት የተመሠረተ አንድነታቸውን ቢጠቃለል ደግሞ የኢትዮጵያን ሀሳዌ ነው። ልክ እንደጠባብ ብሔረተኞች ኢትዮጵያን ለማዳን መጀመሪያ ማወላለቅ፥ ማፈራረስ፥ በየብሔረሰቡ ነጣጥሎ ማደራጀት ማለትን ከተያያዙት ቆይተዋል። ይህ አመለካከት "አንድነት" በተባለ "የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት ልሣን" ቁጥር3፥ 1ኛ ዓመት ግንቦት 27 ቀን 1986 ዓም "መዐሕድ ወደጎብረ ብሔራዊ ፓርቲ ለምን አልተለወጠም" በሚል ርእስ እንዲህ ሲባል ተጽፎ ተገልጧል፦

"የአማራው ተራማጅ ትውልድ ለውድ ሀገሩ መበታተንና እጅግ አሥጊ የመድከም ሁኔታ ላይ መገኘት ምክንያት ሊሆን በቅቷል። ... ስልቱ የተወናበደና ችግርን ያረገዘ መሆኑን ባለመገንዘብ የዚህ ጉሣ የዚያ ብሔረሰብ ሳይል በጎብረ ብሔራዊ አቋም በጋለና በነደደ የትግል ስሜት ለዓላማው የተሰዋና የተማገደ ትውልድ ነበር። ..." ይልና

"... እንድ መንጋ ሲነዱት የነበሩት ጥቂት የኤርትራና የትግራይ "ተራማጆችና ግንባር ቀደም ታጋዮችን' ደባና መሠሪ ተንኮል በወቅቱ ሊገነዘብ አልቻለም። ... የግምገማው ሁሉ መደምደሚያ አንድ ጭብጥ ይመስለናል። ደግሞ መታለል፥ ደግሞ መበለጥ፥ ደግሞ መዘናጋት መቆም ይኖርበታል።" ብሎ ዝቅ ይልና ደግሞ:

"የጊዜው ፖለቲካ ደግሞ ... ጉሣና ክልልን ሃይማኖትን ... መሠረት ያደረገ እንዲሆን ተደርጓል። ... በዚህ ተጨባጭ ሁኔታ በጎብረ ብሔር የፖለቲካ አደረጃጀት ሕጋዊ በሆነ ሁኔታ አመርቂ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለማከናወን አልተቻለም" ይላል።

አንባቢ ሐሳቤን በትክክል እንዲረዳልኝ እፈልጋለሁ። ታዲያ እንዳልሰለች እየለመንኩ አንድ ነጥብ ደጋግሜ ለመግለጥ እውዳለሁ፦

የማንም ኢትዮጵያዊ ግለሰብ የአንድ ብሔረሰብ ተወላጅነቱ፥ ከዚያ ብሔረሰበ ቋንቋ፥ ባህል፥ ወግና ልማድ ... ጋር ያለው ስሜታዊና መንፈሳዊ ግንኙነት፥ ስነልቦናዊ ትሥሥር ... በአጠቃላይ ብሔረርተኛነቱ ከሌላው ግንዛቤው - ከኢትዮጵያዊነቱ በልጠበትና ተሽሎት ካገኘው በዚያው በሚያምንበት ብሔርተኛነቱ መሠረት የመሰባሰብ፥ የመደራጀት መብቱን አከብርለታለሁ፤ እንዲታወቅለትና እንዲከበርለትም ያስፈልጋል አላለሁ። ነገር ግን ማንኛውም ብሔርተኛ ራሱ አምኖ መመሪያውም ያደረገውን ብሔርተኛነት (ጠባቡም ዓይነት ይሁን አክራሪው) እንድብቸኛ አማራጭ፥ እንደትክክለኛው ግንዛቤና የትግል መንገድ አድርጉ በሌላው ላይ ለመጫን ሲሞክር ፈር ለቀሃል ሊባለው ይገባል። ***የአማራው ብሔርተኛነትም ሆነ የሌሎችን በተመሳሳይ የመደራጀት መብት እያወቅን - ግን በጉላ ድምፅ በብሔርተኛነት ተደራጅቶ ጎብረ ብሔራዊቷን ኢትዮጵያ ማዳን አይቻልም እንላቸዋለን።*** ጉዳዩ "ከዝንጀሮ ቆንጆ ምን ይመራርጡ" ነው።

የማንኛውም ብሔረሰብ ድርጅት ኢትዮጵያዊነትን አይወክልም። ብሔረሰቡ በቁጥር ይነስ ይብዛ፥ በአሠፋፈሩ ይጥበብ ይስፋ - በብሔረሰብ ስም፥ አስተሳብና እምነት ላይ ተመሥርቶ እስከተደራጀ ድረስ አሰያየሙና አስተሳሰቡ፥ ባህሪው ተግባሩ ... ከመጠሪያው ጋር የሚሳሳቡ፥ ውስጣዊ እንቅስቃሴውና የፖለቲካ ህይወቱ ያንኑ ዓይነተኛ መከሠቻው የሆነውን ብሔርተኛነት የሚያጠናክሩ እየሆኑ ጉዞውን ነው የሚቀጠለው። እስካሁን በተመዘገበው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ

ውስጥ እንደተመለከትነው የብሔረሰብ ድርጅቶች ባለፉት ሦስት ዓመቶች ብት ብለው ከደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ደሞክራሲያዊ ድርጅት በስተቀር ከዚያ ብሔርተኛ አስተሳሰባቸው ሊወጡ ቀርቶ ይባስ ጠባብ ወይም ይበልጥ አክራሪ እየሆኑ ነው የሚመጡት። ስለዚህም ዛሬም ወደፊትም ጎብረ ብሔራዊቷን ኢትዮጵያችንን ለማዳን ያለን አማራጭ፦

ሀ በዓላማችን የመላ ኢትዮጵያን ሕዝብ መብት ለመጠበቅ፥ ጥቅሙንና ፍላጐቱቱ ለማራመድና ለማሟላት፥ ለአንድነትና ለእኩልነቱ ሰንቆም፥

ለ በይዘት የተለያዩ ብሔረሰብ ተወላጆችን አሰባስ
በንና አደራጅተን በእርግጥም ኢትዮጵያዊነትን
ኅብረብሔራዊነትን ስናንፀባርቅ ኢትዮጵያዊ ባህሪ
ያችን ከይዘታችን ጋር ሲደጋገፍ፥
ሐ በአሰያየም ጭምር ብቸኛ መግለጫና መተዋወቂ
ያ የሆነውን ኢትዮጵያን የያዘ መጠሪያ ሲኖረን፥
መ በዕለት ዕለት ተግባራችንና የፖለቲካ እንቅስቃሴ
ያችን እንወዳታለን የምንላትን ሀገር ሕዝቦች አቀ
ራርቦ ወንድማማችነታቸውን እንዲፀና ኅብረታቸ
ው እንዲጠበቅ ስናደርግ ነው::

በተግባር፥ በዕለት ተዕለት የፖለቲካ ሥራችን ጠባብ ወይም አክራሪ ብሔረተኛነትን የምናስፋፋ ከሆንን የኢትዮጵያዊነት መከሠቻ የነበሩትንና የሆኑትን ተቋሞች፥ ድርጅቶች፥ ግንኙነቶች ካላስከበርን፥ ካላከብርን፥ ካልተንከባከብን በእኔ እምነት ኢትዮጵያዊነትን በመቦርቦር፥ በማዳከም በመገዝገዝ እንደተሠማራን ነው የምመለከተው:: እኒያን በአዲስ መልክ ኢትዮጵያዊነትን በኅ/ብሔር ማኅበሮች፥ የፖለቲካ ድርጅቶች አማካኝነት በርዕዮተ ዓለም፥ በፖለቲካ እምነትና ፕሮግራም ስለአዲሲቷ ኢትዮጵያ ባላቸው የጋራ አመለካከትና ግንዛቤ ተሣስረው ... የኅብረ ብሔሪቷ ኢትዮጵያን ህላዌ እያንፀባረቁ ይወክሉ የነበሩትን ኃይሎች በሚመለከት ደግሞ ወደኋላ እየተመለሱ የጋራ ታሪካቸውን በክህደት መለወስ ምን ይባላል? እማንኛውም ኅ/ሰብ ውስጥ በማንኛውም ሀገርና ወቅት የአንድ የፖለቲካ ድርጅት፥ የኅብረተሰብ ክፍል አባል የነበረ/ የሆነ ግለሰብ በሌላ ሁኔታ የፊት እምነቱን ሊለውጥ ይችላል:: የሚለውጠው በተመልካቹ መሥፈርት ወደከፋ ወይም ወደተሻለ መንገድ የሚወስደው ሊሆን ይችላል:: በዓለም አቀፋዊነት ያምኑ ከነበሩት የአክራሪ ወይም የጠባብ ብሔርተኛነት አቀንቃኝ የሆኑብን አሉ! በጣሊያን ጊዜ የኢትዮጵያዊነት ስሜት ተንኖ ጠፍቶባቸው ለጠላት ባንዳነት አድረው አርበኞቻችንን ቢያይነቱ የጐዱ በርካታ ነበሩ:: ኢትዮጵያ ሀገራችን በጣም ዥጉርጉር ነች:: ታዲያ ጥቂት ግለሰቦች እየከዱ የጠላት መሣሪያ ስለሆኑ ... በጅምላ እነሱ የነበሩበትን ማኅበር፥ ድርጅት፥ የኅ/ሰብ ክፍል፥ ትውልድ ልናወግዝ አይገባንም:: አለዚያ ትልቅ ስህተት እንፈጽማለን::

የትግራይና የኤርትራ ወጣቶችን ታሪክ ስንመረምርም የጅምላ ውግዘትና ጥርጣሬ ተገቢም፥ ልክም አይደለምና በጣም መጠንቀቅ ይኖርብናል:: ያ "... ጥቂት የኤርትራና የትግራይ 'ተራማጆችና ግንባር ቀደም ታጋዮችን' ደባና መሠሪ ተንኮል በወቅቱ ሊገነዘብ ... " ያልቻለው የአማራው (ለምን አብረው ተነጂ የሆኑት የሌሎቹ ብሔሮች ተወላጆችስ አይጠቀሱም!) ተራማጅ እንደመንጋ ተነድቷል ማለት የዚያን ትውልድ የአንድነትና የጋራ ትግል ታሪክ ይክዳል:: የትውልዱ ወጣቶች አልነበሩም በዘር የተሰባሰቡት:: ሁሉም የትግራይ ወጣቶች፥ ተላላዎች፥ ቅኖች፥ ... አልነበሩም፤ አይሆኑምም:: የሁሉም ብሔረሰብ ተወላጆች መካከል የተለያዩ ባህሪዎችና አቋሞቻቸውም የተለዩ ነበሩ:: ከትግራይና ከኤርትራ ወጣቶች እነብርሃነ መስቀል ረዳ፥ ዮሴፍ አዳነ፥ መስፍን ሃብቱን፥ ዐባይ አብርሃን፥ ኃይሌ ዐባይ፥ ፀሎተ ሕዝቅያስ፥ ዘርዓብሩክ አበበን፥ ተስፋዬ ደበሳይ፥ ገ/እግዚአብሔር፥ ገለብ ዳፍሳ፥ ጠባብ ብሔረተኞች ነበሩ፥ የጠባቦችን ዓላማ ለማራመድ ሠራውን የኢትዮጵያ ተራማጅ ትውልድ "በተንኮልና በመሠሪነት" እየነዱት ነበር ... ማለት ሀሰት ነው:: ከዚያ ትውልድ ተራማጅ ክፍል ውስጥ እየተቀራረቡ መጥተው በርዕዮተ ዓለምና በፖለቲካ አቋማቸው ተመሳሳይነትና አንድነት አግኝተው በድርጅት (ማኅበርም ፖለቲካዊም) አማካኝነት ተጨባጭ ጥምረትና ህላዌ ሰጥተው ነበር ከተለያዩ ብሔረሰቦች የተወለዱት ኢትዮጵያውያን (አማሮች ትግሬዎች፥ ኦሮሞዎች፥ ጉራጌዎች፥ ወላይታዎች፥ ሲዳማዎች፥ አገውዎች ... ሌሎችም! ሌሎችም፤) አብረው የታገሉት፤ የተጨፈጨፉት፤ እየታሠሩ የተሲቃዩት፤ የተሰደዱት:: የዚያው ትውልድ አባላት የሆኑ በኢትዮጵያዊ ጽኑ እምነታቸው እስከዛሬ እየታገሉ ያሉም የተለያዩ ብሔረሰብ ተወላጆች የማይታበል ሀቅ ነው::

አማሮች ብቻ አይደሉም ዛሬ ለኢትዮጵያ ህላዌ በመቆም ጠባብ ብሔርተኞችን - ህወሃትን፥ ሻዕቢያንና መሰሎቻቸውን ተቃውመው እየታገሉ ያሉት:: *ለኅብረራዊት ኢትዮጵያ ታግለው፥ በፋሽስቱ ደርግ አብረው ታጭደው፥ በሠፌ ጉግድጓድ ውስጥ ክምር አስከሬናቸው አንድ ላይ ተቀብሮ፥ የጋራ እምነታቸው ቁርባን ሆኖ እስከመቃብር ያደረሳቸውን፥ አካላቸው አብሮ ማሙቶ አፈር የሆነውን የዚያን ትውልድ ተራማጆች ፈፃዳላዊ አሻራውን ባልቀረፈ አክራሪ ብሔርተኛነት ዛሬ አትለያዩባቸው! የገለባ ክምር አይደለምና ያንን የጋራ ታሪካቸውን እየናዳችሁ አታልከስከሱት!*

አፍራሾቹ ጠባብ ብሔርተኞች እኮ "የኢትዮጵያ ጉዳይ አይመለከተንም፥ ቀድመን ይኸን ብሔር፥ ያንን አካባቢ ነፃ እናውጣ ብለው ከዚያ ትውልድ ተራማጅ ክፍል ጋር በስፋት አብረው አልተራደራጁም:: በተማሪው እንቅስቃሴ ውስጥ ገባ ብለው የነበሩትም ብዙ አልገፉም:: የግራውን ርዕዮተ ዓለም ቀድመው የተቀበሉት ደግሞ ያለጥርጥር በኢትዮጵያዊነታቸው የሚያምኑት ተራማጆች ነበሩ:: ጠባብ ብሔርተኞች ርዕዮተ ዓለሙን እንደካባ ያጠለቁት በኋላ ነው:: ያውም ያቺን "... እስከመገንጠል" የምትልዋን ሀረግ ስላዩ::

ህወሃት፥ ሻዕቢያ፥ መሰል ጠባቦች በኢትዮጵያውያን ላይ ዛሬ የጫኑብን የዘር ፖለቲካ ሁሉንም ነገር በዚሁ በዘርኝነትና በጐሠኝነት ጐራ እንድንመለከተው እየጋበዘን፥ በተሳሳተ መንገድ አገራችንን ለማዳን ወደማያስችል እየገፉን ነው:: ያ ኢትዮጵያን አሻሽላለሁ ብሎ - በሙሉ ስሜት፥ እምነትና ቁርጠኝነት ወቅቱ በጠየቀው ፀረ ውዳል

የዴሞክራሲያዊ አብዮት ትግል ውስጥ የገባው ኢትዮጵያዊ ተራማጅ ክፍል ያደረጋቸውን አስተዋፅዖዎች አወነታዊና አሉታዊ ገጽታዎች በጽሞና መገምገም ሲገባ ያልሆነ ትርጉም፥ ያለሆነ ዓላማ፥ ያልሆነ ታሪክ መስጠት ግን አይገባም።

እነዚሁ አፍቃሬ ፊውዳል የሆኑት አክራሪ ብሔርተኞች ክፍል መረን የለቀቀ ዘመቻ በመቀጠል "... ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌለው፥ ጭካኔን፥ ክህደትን፥ ሸፍጥን መመሪያው ያደረገ፥ ..." ብለው ከሞራላዊ አቅጣጫም ሌላ የትግል ግንባር ሊከፍቱበት ይቃጣቸዋል። *(አንድነት ቁ.3 ግንቦት 27 1986 ዓም- የመዐሕድ ልሳን)* እስቲ መለስ ብለው ቀደም ባሉት እነሱ በሚያወድሷቸው ፊውዳላዊ ገዢዎች የተፈጸመውን ጭካኔያዊ ተግባሮች ያገናዝቡ። ሥፍራ እየጠቀስን፥ ስም እያነሳን መከራከር እንችላለን። በአክራሪዎች መመዘኛ "ፈሪሃ እግዚአብሔር አድሮባቸዋል" የሚባሉት ፊውዳሎች የሠሯቸውና አሁንም ሌሎች አማኞች እየሠሯቸው ያሉት የግፍና በደል ቁልሎች በምን መመሪያነት ይሆን የተፈጸሙትና እየተፈጸሙ ያሉት ብሎ መጠየቅ ተገቢ ይሆናል። ስለነፃነት ትንሽ ግንዛቤ ካላቸው የሰው ልጆች (ኢትዮጵያውያንም) በፈለጉት የማመን፥ ወይ በምንም ያለማመን መብታቸው ሊከበርላቸው ይገባል።

በእግዜር ያላመነ ኢትዮጵያዊ መኖር የለበትም የሚሉ አክራሪ ብሔርተኞች ወይ ሃይማኖተኛም/(ክርስቲያን፥ እስላም ወይም ሌላ ጭምር) የመሆን መብታቸውን እኛ እናከብራለን። ነገር ግን እኛ ለዴሞክራሲ ስለሆነ የምንታገለው የወደፊቷ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ውስጥ እምነትን በግድ መጫን ሥፍራ ሊሰጠው አይገባም እንላለን። የሐሳብና የእምነት ነፃነት ወሰኑ ሠፊ ነውና። በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ የግለሰቡን የእምነት ምርጫ ኅ/ሰቡም መንግሥትም ማክበር አለበት። የማንንም እምነታዊ የምርጫ መብት ለመንካት መብት የለውምና።

የአክራሪ ብሔርተኛነት አቀንቃኞች ነባራዊውን የኢትዮጵያ ሁኔታ (ያመጣጥ አቅጣጫ የተለየ ይሁን እንጂ) ልክ እንደጠባብ ብሔርተኞች ያውገረግሩታል። የነበረውን የብሔር ጭቆና እንደሚክዱ ቀደም ብዬ አሳይቻለሁ። ሁለተኛ የተወሰኑ የአንድ ብሔረሰብ ልዩ ጥያቄዎችን በማቀንቀን ወይም የብ/ሰብ ጭቆናን ለመቃወም፥ አለዚያም ለመገንጠል፥ ወይም ከሌላ የጐረቤት ሀገር ጋር ለመቀላቀል፥ ... በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም በሌላው ብሔረሰብ ላይ የተመሠረቱ እንቅስቃሴዎች የተጀመሩት ኢትዮጵያ ውስጥ የግራው ኃይል ገና ሳይፈጠር፥ ገና ሳይደራጅ፥ ወይም ገና በማቆጥቆጥ ላይ እያለ ከግራው ሚናና ተፅዕኖ ውጭ ቢሆንም ተራማጁ ትውልድ የፈጠረው ያስመስሉታል። የኢትዮጵያ ግራ የብሔረሰብን ችግር አልፈጠረውም። የየብሔረሰቦቹ የፊውዳል ገዥ መደቦች ጭቆና፥ የኢምፔሪያሊስቶች "ከፋፍለህ ግዛ" ፖሊሲ፥ የዴሞክራሲ አለመኖር፥ ዕኩልነትና ፍትኅ ርትዕ መጥፋት እንጂ።

. በሀገራችን በስተምሥራቅ በእንግሊዝ ወታደራዊ አስተዳደር ሥር በጅጅጋና በሃውድ ባንዲራ ሰቅለው ያነቀሳቅሱት የነበረው የሶማሊያ ወጣት ክንፍ (Somali Youth Leage)፥
. በኤርትራ ምዕራባዊ ቆላማ አካባቢ እንቅስቃሴ ጀምረው የነበሩት በኋላ በኤርትራ ሓርነት ግንባር የተጠቃለሉት ክፍሎች
. ከአሁኑ ወያኔ በባህሪው የተለየ ቢሆንም ጀማሪው የወያኔ እንቅስቃሴ በትግራይ፥
. የሜጫና ቱሉማ/ኦሮሞ እንቅስቃሴ በሸዋና ሌሎችም የኦሮሞ አካባቢዎች (በኋላ በከፊልም ቢሆን የባሌን እንቅስቃሴ ለማስነሳት እርሾ የለገሠው እሱ ነው) አነሱም በዙ ሌሎችም የሚጠቀሱ የብሔረሰብ እንቅስቃሴዎች የዚያ ተወቃሺና ተከሣሽ ጀግና ትውልድ ተራማጀ ክፍል ገና የግራውን ርዕዮተ ዓለም መመሪያው አድርጉ ከመደራጀቱ በፊት ነበር።

በሀገራችን ውስጥ የነበሩት አሁን በድርጅቶች መሥራች አባላት እየተገለጠ ያለውን ስንመረምር ጀማሪው የግራ ፖለቲካ ቡድን (መኢሶን) የተቋቋመው በ1960 ዓም ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ (ኢሕአፓ) የተቋቋመው በ1964 ዓም ነው። እኔ እሰከማውቀው ድረስ የመጀመሪያውን የግራ ቡድን አስኳል በሀገር ውስጥ ያፈራው (The Crocodile Society) ብሎ ራሱን ይጠራ ከነበረው ብርሃነ መስቀል ረዳን፥ ገብሩ ገብረወልድን፥ ዘሩ ክህሸንን፥ ተካልኝ ወልደአማኑኤልን፥ ... ወዘተ የያዘ ቡድን ብቅ ያለው በ1956-57 (እኤአ 1963-64) ነበር። እሱም ግፋ ቢል ያልተጠናከረ የጥናት ቡድን፥ በወቅቱ ይለጥፉት ከነበረው "የስብሰባ ...ወዘተ" ማስታወቂያቸው ስንመለከት ደግሞ ያውም አብዮታዊ ትግል የማካሄድ ተግባርን ገና በውል ያልጀመረ ቡድን ነበር። አክራሪ ብሔርተኞች የፊውዳል ገዥዎችን የጥፋት ዝርክርክነት፥ የፈጠሩትን የፖለቲካ ውጥረት አላልቶ ሊለውጥ የተፋለመ ወጣት (ያኔ) ትውልድ፥ ከዚህም በተለይ ከትውልዱ ውስጥ ተራማጅ፥ ግራ ለተባለው ክፍል ሲያሸከሙት እንሰማለን- እናነባለን። ይህ ልክም፥ ተገቢም አይደል- ቢፈለግም እነሱ እንደሚሉት ሊሆን አይቻለውም። በሀሰት ክስ የሌሎችን ስም ማጥፋት ብስለትን አያሳይም፥ ሥርዓትን የተከተለ ዘመናዊ የፖለቲካ ትግል ስልትም አይደለም። ሥፍራው ከፊውዳላዊ አሉባልታ ሠፈር ነው።

ለምሳሌ የኤርትራው ትግል እንዴት ነበር የተጠናከረው ብንል ሁለቱ ጉልህ ምክንያቶች

ሀ የአፄ ኃይለሥላሴ ፊውዳላዊ አገዛዝ ኤትርትራው ያን በተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ ያገኙትን "በኢትዮጵያ ውስጥ ፌዴራላዊ ግንኙነት" ደረጃ

(Status)÷ የውስጥ አስተዳደር መብት÷ በኤርትራ ውስጥ የኗሪዎች ሀሳብ የመግለጥ÷ የመደራጀት÷ የመምረጥና የመመረጥ÷ ... ወዘተ መብቶች ባለ ማክበሩ÷ በኋላ ደግሞ

ለ እንቅስቃሴ ሲጀምሩ በሰመቃና በጦርነት ብቻ ተቃውሞውን ለማጥፋት መሞከሩ ናቸው::

በእርግጥ የዐረብ መንግሥታትና የምሥራቁ ዓለም በእጅ አዙርና በቀጥታ ግንባሮችን መርዳታቸው ለብሔርተኞቹ መጠናከር ትልቅ አስተዕያ አድርጓል:: አስከምናውቀው ድረስ የሜጫና ቱሉማ ማኅበር የመጠጠል ጥያቄ አልነበረውም:: በውቅቱ በኦሮሞ ሕዝብ ላይ የነበረውና የመደብና የብሔር ጥምር ጭቆናን ለማስወገድ ህይወታቸውን ለማሻሻል ግን የንጉሡ ፈውዳላዊ አገዛዝ ያደረገው ጉልኅ ነገር አልነበረም:: በወቅቱ የነበረው በንጉሡ መልካም ፈቃድ የተቋቋመ ፓርላማንት የጢሰኞችን ጭብር የሚቀንስ ረቂቅ ቀርቦለት እንኳ ሊየፀድቅ አልቻለም:: አሁንም ወደሰመቃው ነበር የዞረው:: ሶጂኔራል ታደሰ ብሩን÷ ሶማሞ መዘምርን ... ሁኔታ ያስታውሷል::

የጠባብ ብሔርተኛው ህወሃት በትግራይ መነሳትና የተካሂደውም ትግል የተለዩ ገጽታዎች አሉት:: በኤርትራ በተለይም ደግሞ በህግሓኤ (ሻዕቢያ) እየታገዘ÷ በትግራይ ውስጥ ትግል የጀመሩትን ኅ/ብሔር ድርጅቶች ወግቶ በማባረርና የትግራይ ነፃ አውጭ ግንባር የተባለውን ሌላ ብሔርተኛ ግንባር ደግሞ ወግቶና አታሉም መሪዎቹን እያየረደ በማጥፋት - አሁን ጎሠኛነትን በድፍን ኢትዮጵያ ላይ ለመጫን የቢቃው ህወሃት/ኢሕአዴግ የብሔር ጭቆና ብቻ ውጤት መሆኑ በጣም ያጠራጥራል::

1 ትግራይ ከትግሪኛ ተናጋሪው በተጨማሪ ሣሆዎች ÷ አገውዎች÷ ኩናማዎች÷ አፋሮች የሚኖሩበት የአያሌ ብ/ሰቦች የሚኖሩበት ክ/ሀገር ነው::

2 ትግራይ ውስጥ ያሉት ብ/ሰቦች በሙሉ በሌሎች ክ/ሀገሮችም ውስጥ ጭምር የሚኖሩ ናቸው:: ትግርኛ ተናጋሪው ከኤርትራው 'ከበላ' ነዋሪዎች (ሐማሴን÷ ሠራዬና አከለጉዘይ) ጋር የተያያዘ የትግራይ-ትግሪኛ ብሔረሰብ ክፍል ነው:: የሳሆዎች ከፊል ጐናቸው ኤርትራ ውስጥ ነው:: አፋሮች ደግሞ በወሎና በሐረርጌ÷ ቀሪው በጅቡቲ ውስጥ ነው የሚኖረው:: ኩናማዎች አብዛኛው ክፍላቸው ኤርትራ ውስጥ÷ የተወሰነው ደግሞ በወልቃይት (ጐንደር) ውስጥ ይኖራል::

ታዲያ ህወሃትን ለሥልጣን ያበቃው ትግል በሁለት ተዋሳኝ አካባቢዎች - በኤርትራና በትግራይ በተለያዩ ወቅቶች ትግል በጀመሩ÷ ተመሳሳይ የመገንጠል÷ "ሶሻሉት" ዓላማ ቢያዙ ሁለት የትግራይ-ትግሪኛ ብሔርተኛ ድርጅቶች አማካኝነት ነበር የተካሂደው:: የትግራይ-ትግሪኛ ብ/ሰብ ክልሎችን ከተቻለ አስፋፍቶ ለመገንጠል የሚያስችል ምሥጢራዊ ስትራቴጂ ይዞ አልቦ ማዕቀብ (Ruthless) የሆነ ቃልኪዳን ያለው ኃይል ሆኖው የታገሉት::

ለጊዜው በኤርትራ ያለውንና ሶብረውን ባጢቃላይ ከውጭ (ባዕዳን) ወረራና ጣልቃገብነት ጋር በአመዛኙ ከምዕራብ ቅኝ ገዢዎች ወረራና ከፉፍሎ የመግዛት ተንኮል ጋር የተያያዘውን ትተን የትግራዩን እንመልከት:-

በትግራይ ክ/ሀገር ላይ ተመሥርቶ የታገለው የትራይ-ትግሪኝ ጠባብ ብሔርተኛ ቡድን

. ትግርኛ የማዕከላዊ መንግሥት መገልገያ ቋንቋ ባለመሆኑ፤

. በምትኩ አማርኛ ቋንቋ ይህንን ሥፍራ በመያዙ÷ ነባሥታቱና ከመሳፍንቱም በርካታው (ምናልባትም እንደዘመነ አጤ ዮሐንስ) የክ/ሀገሩ ተወላጆች ባለመሆናቸው

. የመንግሥት ማዕከል መጀመሪያ ወደጐንደር በኋላም ወደሸዋ (አንኰበር÷ አዲስ አበባ) በመሸሹ ፈውዳላዊ መደብ ውስጥ የትግራይ-ትግሪኝ የበላይነት ባለመጠበቅ ወይም በቁጥርም በሌሎችም የወቅቱ መሥፈርቶች አማራው በመብለጡ÷

. እንደዘመነ መሳፍንቱ ድርሻን ለማሳደግ ወይም ቆርሶ ዞር ለማለት ካልሆነ በስተቀር ትግራይ ትግሪኝ ብ/ሰብ ብዙ የተነሳው ነገር አልነበረም:- ዘውድ እኮ ትንሽ ነገር አይደለም ካልተባለ በቀር ርግጠኛ ዓላማው ሌላ ስለሆነ ነው::

በእኔ አስተያየት እንደኢትዮጵያ ባሉት በኢኮኖሚም ሆነ በሌሎች የልማት መስኮች ኋላቀር በሆኑት ሀገሮች የመደብና ብሔር ጣምራ ጭቆና ዋና መሠረት የሆነው የመሬት (በተለይም ገጠር) ሀብት ባለንብረትነት ነው:: በሀገራችን ክፍሎች ከከፊል ሸዋ ጀምሮ በምዕራባዊ ደቡባዊና ምሥራቃዊ ክፍሎች መሬት ከአርሶ አደሮች ተቀምቶ ለመሳፍንቱ÷ ለወቅቱ ፈውዳላዊ መንግሥት ሹማምንት÷ መኳንንትና ወታደሮቻቸው (ነፍጥ የታጠቁ ሠፋሪዎችና ፀጥታ ጠባቂዎች)÷ ለባላባቶች (አማሮች÷ ትግሬዎች÷ አሮሞዎች÷ አገውዎች÷ ጉራጌዎች ... ሌሎችም የተካተቱበት) መሰጠቱ ህቅ ነው:: የመደብ ብሔር ጣምራ ጭቆናው መሠረት ይኸው ነው:: በትግራይ ውስጥ ግን "የአማራው" ወይም የ'ሸዋ አማራ" ገዢዎች የሚባሉት መሬት (የማንንም) አልቀሙም ነበር:: በባህልም ረገድ በተለይ አማራና ትግራይ-ትግሪኝ በአመጋገብና አለባበስ÷ በሀዘንና ደስታ መግለጫዎች÷ በሃይማኖታዊ ሥርዓት ተወራራሽ ናቸው:: አንዳንዱም የጋራ በመሆኑ የባህል ጭቆና የሚባለው የትግርኛ ቋንቋ ከአማራው ዕኩል በሀገር ደረጃ ይፋ የመንግሥትና የንግድ መገልገያ ካለመሆኑ ውጭ ልዩ ጭቆናና እገዳ እስካልተደረገበት ድረስ ብዙ ተጨባጭ ነገር ማየት ያዳግታል:: የአማርኛ

ተናጋሪው ከትግርኛ ተናጋሪው መብለጥ፥ አማርኛ ይበልጥ ከሌሎች ብሔረሰቦች ጋር ተሰባጥሮ መገኘት (ቢታሪክ አጋጣሚ) እና በደቡብና በምሥራቅ የኢትዮጵያ ቀጥጥር ሲጠናከር በገዢው የፊውዳል መደብ ጥምር ውስጥ አማርኛ ተናጋሪው የበላይነት ይዞ መገኘት ... አሁን ሊያዘው ቀዳሚነት ዋና ዋና ምክንያቶች ይመስሉኛል።

በመፈራረቅም ሆነ በመጣመር የአማራውና የትግራይ ትግሪኛ ብሔረሰቦች ተወላጅ የሆኑት ክፍሎች (ብቻቸውንም ባይሆን) በገዢው መደብ ውስጥ የበላይነት ይዘው ይህንኑ በፖለቲካ ሥልጣን፥ በኢኮኖሚ ጥቅም የጋራቸው በሆነው የአማራ ትግራይ-ትግሪኝ ባህል ... መልክ ሲገልጡና ከሌሎች የኢትዮጵያ ብ/ሰቦች ሠፊ ሕዝብ ጋር ደግሞ የመደብና ብሔር ጣምራ ጭቆናን የሚያሳይ ግንኙነት ፈጥረው ኖረዋል። አንዱ ሌሳውን ከሶ ለመውቀስ በሚያዳግተው ውስብስብ ግንኙነቶች ውስጥ ነው የኖሩት። ህወሃት/ኢሕአዲግ ከቀድሞው የገዥ መደብ ጥምር ውስጥ አማራውን ነጥሎ ማውገዝ፥ በሌሎች ብ/ሰቦች ተጠልቶ የበቀል ሰለባ እንዲሆን ማድረግ፥ በአዲስ የትግራይ-ትግሪኝ የገዥ መደብ እጅ የፖለቲካ፥ የኢኮኖሚ፥ የቋንቋም የበላይነት ለማስገባት ወይም በዚሁ መደብ አማካኝነት ኢትዮጵያን አፈራርሶና አጥፍቶ ሌላ "ሠፊና ጠንካራ" የትግራኝ-ትግሪኝ መንግሥት በሀገራችን በስተሰሜን ለመፍጠር ነው።

በአፄ ኃ/ሥ ዘመን በትግራይና በኤርትራ ውስጥ በቂ የልማት ሥራዎች - መንገዶች፥ የሐኪምና ት/ቤቶች፥ ፋብሪካዎች ... አልተሠሩም የሚባለውም መሠረት ይዞ በተጨባጭ ማስረጃ የብሔር ጭቆናን ኢያሳይም። የትግራይ-ትግሪኝ ብ/ሰብ አብረውት የሚኖሩ ሌሎች ብ/ሰቦችንም እየጨቆነ ነው ተብሎ ሊከሰስ ከሚችባልባቸው ክ/ሀገሮች አንዱን ትግራይን ብቻ ነጥለን እንመልከት። ከሕዝቡ ብዛት አኳያ "የአማራ" ክልል እየተባሉ ከሚጠሩት ከጉንደር፥ ጐጃም፥ ከፊል ወሎ ጋር ሲወዳደር እንደክ/ሀ ያገኘው ድርሻ የተሻለ እንጂ ኢያንስም። በእርግጥ ሽዋ ላይ የሰረረው ትኩረት ሌሎችን ክ/ሀገሮች እያስቀና ያበሳጨ ጉዳይ ነው። እኔ የዚያ መንግሥት የልማት እቅዶች በፍትሐዊ መንገድ ነው በሙሉ የተሠሩት አልልም። ሆኖም ግን በተለይ "አማራውን እንደብ/ሰብ ለመጥቀም" የተደረጉ ቢሆኑ ኖሮ ጉንደር ጐጃም፥ ከፊል ወሎም የበለጠ በለሙ ነበር። ባጠቃላይ የቀደሞ ፊውዳላዊ ገዥዎቻችን አርቀው ማየት ካለመቻላቸው፥ ከአንዳንዶች የሥልጣን ብልግናና "የራሴ" ዮሚሉትን ጠባብ አካባቢ ምላማትና የመጥቀም በዚያውም ራሳቸውን የመጥቀም ፍላጐት መነባትን እንዳስከተለ እገምታለሁ።

ለማጠቃለል የግራው ኃይል ተደራጅቶ ማድረግ በጀመረው እንቅስቃሴ በሀገራችን ሁኔታዎች ላይ ተጽእኖ ማድረግ ከመጀመሩ በፊት ነበር የብሔሮች ጥያቄ በእንቅስቃሴ መልክ የነበረው። ከትግራይ ትግሪኝ እንቅስቃሴዎች በስተቀር በሌሎች ክፍሎች የተነሱት ሁሉ ከብሔርና መደብ ጣምራ ጭቆና የመጡ ናቸው። በኤርትራም የተነሳው ብሔርተኛ እንቅስቃሴ በአመዛኙ የኢትዮጵያ ፊውዳላዊ ገዥዎች ፌዴራሽኑን ማክበር ስለተሳናቸው ነው። የትግራይ ጠባብ ብሔርተኞች ትግል ግን ጭቆናን የማስወገድ ጣጣ አይደለም። ዓላማው፦ በኤርትራ የሚታገለውን የትግራይ ትግሪኝ ብ/ነብ ንዑስ ክፍል አግዞ ዓላማውን በማሳካት የቀረችውን ኢትዮጵያ አፈራርሰው ትግራይንም በመገንጠል አንድ የሠፋና የጠነከረ (ከበጌምድር ከፊሉም፥ ከመሉ ከፊሉን፥ አፋርን ያጠቃለለ፥ አሁን ከመህል ሀገር በመዝረፍና በልማትም ለትግራይ ቅድሚያ በመስጠት እንደሚያሳዩት) አጋብቶ የትግራይ ትግሪኝን ግዛት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ለመመሥረት፥ አለዚያም የትግራይ ትግሪኝ የበላይነት የተረጋገጠባት ደካማ የሆነች ሰሜኑን (ኤርትራን) የምታገለግል ኢትዮጵያን ለመሰየም ከመሆን አይዘልም። በእርግጥ ከዚያ ደሞ ባመቻቸው ጊዜ የሚጠቃለለብትን ከፊሉን ግዛታቸውን (ኤርትራን) እንዲሁም ትግራይን በተለያየ ሰበብ ቅድሚያ ሰጥተውና አጠናክረው እስኩተፈለገው ለመቀጠልም ነው።

ውጫዊ ምክንያቶች አስመልክቶ አንዴ የምሥራቅ ሀገሮች፥ ሌላ ጊዜ የምዕራብ ሀገሮች፥ እንዲሁም የዐረብና አስላማዊ ሀገሮች የአጋዥነት ሚና ሶስረው ቢሆንም በአመዛኙ በኢትዮጵያ ውስጥ የብሔሮች ትግል የተጠናከረው በውስጣዊ ምክንያቶች ነው። የቀድሞው ፊውዳላዊ የገዥ መደብ በጥገናዊ ለውጦች እንኳን ያንን አስከፊ የመሬት ሥሪት በወቅቱ ሳያሻሽል ሌሎችንም የመደብ-ብሔር ጭቆናዎች በመቀጠሉ፥ ጥያቄዎች ከዚያም ተቃውሞውችም ሲነሱ ደግሞ በዕመቃና በጭፍጨፋ ብቻ ለመፍታት በመሞከሩ ነው ሁኔታዎች ያመቻቸው። በደርግ ዘመን ደግሞ መሬት ከቀድሞው የገዥ መደብ ቢወሰድም ለአራሹ በንብረትነት ማስረከብ ሲገባው በመንግሥት እጅ ቆየ። በገበሬ ቀበሌ ማኅበር ሹማምንት አማካኝነት አርሶ አደሩ ለአዲስ ዓይነት ችግሮች ተዳርጉ ሕዝቡ ዴሞክራሲያዊ መብቱ ተነፈገው። ዕመቃና ጭፍጨፋ በመቀጠሉ ሠፊራ መንደር ምሥረታ በኃይልና በግዳጅ ሕዝቡ ላይ ተጫኑ፣ ... እናም ትግል ለጀመሩት ለብሔርተኛ ድርጅቶች ሁኔታው ተመቻቼላቸው። አንዳንዶቹ ጠባብ ብሔርተኛ ድርጅቶች ደግሞ በተጨማሪ ተፈጥሮ ባስከተለው ድርቅ፥ ረሀብና የገበሬው ህይወት መፈናቀልን በመጠቀም (ከውጭ የተለያዩ ርዳታዎች፥ ከውስጥ ደግሞ በውትድርና የሚሠለፍ በገፍ በማግኘት) ይበልጥ ለመጠናከር ቻሉ።

የዚያ ኢትዮጵያዊ ትውልድ ተራማጅ ክፍል በዘርና በጐሣ የሚያምን አልነበረም። ይልቁን በዓለም አቀፋዊነት አጥብቆ ያምን ነበረ እንጂ። ጠባቦችም ሆኑ ሌላ ዓይነት ብሔርተኞች ከዚያ ተራማጅ ክፍል የአስተሳሰብ ይዞታ በጣም የተለዩ ነበሩ። በኋላ ለዚያ ጎጠኛ ትግላቸው

ይጠቅማል ያሉትን ከማርክሲዝም-ሌኒንዝም ውስጥ መለቃቀም ቢጀምሩም አስተሳሰባቸው ቀጥታ ጎጠኛና ክልልተኛ እንደሆነ ነው የዘለቀው። ህወሃት በአንድ ወቅት ለጠባብ ብሔርተኛ ዓላማው ማራመጃ በሶቭየት ጎብረት የነበረውን የይሁዶች (ቡንዶች) ድርጅት በማሙነከሪያነት አንስቶ ነበር። ከማርክሲዝም ሌኒንዝም ውስጥም "... እስከመገንጠል" የሚለውን ነው ጨርፈድ አድርገው የወሰዱት። በኋላም የጎሠኛ "ማርክሲስት" ቡድኖች ሊግ (ከዩጉዝላቪያው የኮሚኒስቶች ሊግ አንድ ምዕራፍ መንትፈው) ነው በኢትዮጵያ መቋቋም አለበት በማለት ሰሚን ያተክሩ የነበሩት። ቢከፍቱት ተልባ-ሆነና ሁሉም በጠባብ የትግራይ-ትግሪኝ ብሔርተኛነት እምነታቸው ላይ ጠንዝተው ስለኖሩ ይኸው ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪኩንና አስከሬኑን ጭምር በዘር በጉሣ፥ በክልል ... በመፈረጅ መከፋፈሉንና መቧታተኑን የተያያዙት።

አክራሪ ብሔርተኞች ታዲያ በክልልተኛና ብሔርተኛ አስተሳሰብ ለራሳቸው የሚቀርቡትን ጠባብ ብሔርተኞች እዚያ ትውልድ ተራማጅ ክፍል ላይ ሊዘንቁ ይጥራሉ። ከሁለቱም ዓይነት ብሔርተኞች በ"ጠበል" እንላለን! የጎብረ ብሔራቷን ኢትዮጵያ ጎላዌና ጎብር የሚያረግፉ የሠይፍ መንታ ስለቶች ናቸውና! የዚያ ትውልድ ተራማጅ ክፍል አንድ የማይፋቅ መታወቂያው ጎብረ-ብሔራዊነቱ ነው!!

ለአክራሪ ብሔርተኛነት አቀንቃኞች ወገኖቻችን መልዕክታችን በያዛችሁት መንገድ፥ በአንድ በኩል "ብሔርተኞች ሀገራችንን በጉሣ እየከፋፈሉ አፈረሷት" እያላችሁ ተገቢ ክስና ወቀሳ፥ የምንታገለውም አንድነቷ ለተጠበቀ ኢትዮጵያ ነው እያላችሁ በዚያው አንደቢታችሁና ቅፅበት ደግሞ "አመርቂ ትግል ለማድረግ የሚቻለው በብሔረሰብ በመደራጀት ነው" ካላችሁ፤ ሀገራችንን እያጠፋ ያለው በብሔረሰብ የመሰባሰብ በሽታ ነውና ሌሎቹ (ጠባቦቹ) መጥፎ - የእናንተ (አክራሪዎቹ) ጥሩ አይሆንም። ነገሩ የአንድ ሠይፍ መንታ ስለት እንደሚሉት ነውና!

ይልቁንስ "አዘለም አንጠለጠለ - ተሸከመ ነው" ይሏልና የጉሣ ፖለቲካ ሁላችንም ነው የሚያጠፋው። "እሺ!" የሚላችሁ ከሆነ በጉሣ የፖለቲካ ጥርጊያ ውስጥ እናንተንም አትንጉዱ፤ መንገዳችሁን ለውጣችሁ ኢትዮጵያዊ አድርጉት እንላችኋለን። ብሔርተኛነት አሮጌና የገለማ በዘርና በጉሣ ላይ የተመሠረተ የፖለቲካ የሥልጣን ሽኩቻ እንጂ አዲስነትና ዘመናዊነት የለውም። በማንኛውም ጎብረ ብሔራዊ ሀገር ጠባቡም ሆነ አክራሪው ብሔርተኛነት የእልቂት ውድመትና ጥፋት መነሾ ብቻ ናቸው። እቀድሞይቱ ሶቭየት ጎብረት ውስጥ ዩጉዝላቪያ፥ ሱዳን፥ ኢራቅና ቱርክ፥ አፍጋኒስታን፥ በጣም በሚሠቀጥጥ መልኩ ደግሞ ሩዋንዳ ውስጥ - ቀደም ብሎ ቡሩንዲ ውስጥ የነበረውም እንደገና ተነሳስቶ አስቀያሚነቱ ቀጥሏል ... ብቻ በእነዚሁ ሁሉ በተለያዩ ብሔረሰቦች ወይም ቋንቋ ተናጋሪዎች ወይም በዚሁ ላይ የሃይማኖት ጉፍጨራ በተጨመረበት ሁኔታ የሚደርሰውን እልቂት በመገንዘብ ኢትዮጵያውያን የዘር ፖለቲካን ጉጂነትና አጥፊነት ማጤን ይገባናል። ከትንንሽ ማ/ሰቦች በቀር አብዛኛው ሶማሊኛ በሚናገርባት ጎረቤታችን ውስጥ እንኳን በጉሣ ላይ በተመሠረተ ፖለቲካና ግጭት በሕዝቡና በሀገሪቱ ላይ የደረሰውን ጥፋት በሚገባ እናጢነው።

አሁን የኤርትራ ሕዝብ የሰላምና የፍትኅ ግንባር መባል የጀመረው ህግሓኤ (ሻዕቢያ) እንኳን በጎሣ መደራጀትና ማደራጀት ከግብረአበሩ ህወሓት ጋር አብሮ ለማጥፋት በፈረዱባት ኢትዮጵያ ላይ ፍቱን ሙግሪያቸው በመሆኑ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ያድርጉት እንጂ በአዲሲቱ (ኤርትራ) ግዛታቸው ውስጥ "በብሔረሰብና በሃይማኖት ላይ የተመሠረቱ ድርጅቶች መሠረት እንዳይኖራቸውም" ብሎ ከልክሏል። ህወሓት/ኢሕአዴግም የግል ርስተጉልቱ ባደረገው ዛሬ ከጉንደርና ከወሎ የተወሰኑ አውራጃዎች ተገምድለው በተጨመሩበት (በተንዘረጠጠው ትግራይ) ውስጥ በሌላ ብ/ሰብና በሃይማኖት ላይ የተመሠረተ ቀርቶ ሌላ የትግራይ-ትግሪኝ ድርጅት እንኳን እንዲያቆጠቁጥ ፈቅዶ አያውቅም። ኢትዮጵያን በተመለከተ ግን "ከሞኝ ሠፈር ሞፈር ይቆረጣል" ሆኗል ነገሩ። ኢትዮጵያን አስመልክቶ ጠባብ ብሔረተኞች ያላቸው ዓላማ ግልፅ ነው:- እንዳያንሰራራ አድርጉ ማጥፋት። አልፎ አልፎ በተለይ ለውጭ ረዳቶቻቸውና ደጋፊዎቻቸው "እኛም እኩ የኢትዮጵያን አንድነት እንፈልጋለን" እያሉ ቢያሽሟጥጡም ዛሬ በዚህ ጉዳይ ላይ ኢትዮጵያውያንን ብዙ ማታለል አይችሉም። በመታለል ሳይሆን ለሆድና ለጊዜያዊ ጥቅም ቅድሚያ በመስጠት ከህወሓትና መሰል ጠባባቦች ጋር የሚያሤሩ የተወሰኑ ኢትዮጵያውያን ቢኖሩም ምንነታቸው ቁልጭ ብሎ በሕዝባችን የታወቀ ነው። አሁን አወዛጋቢው ችግር የአክራሪ ብሔርተኞች ጉዳይ ነው፤ በቃላቸው አንድነትን ከማንም ባላነሰ እየሰበኩ በግብራቸው ግን ያንኑ የብሔረተኛነት ሌላ እትም፥ ሌላ ገጽ ሌላ ጠርዝ ሌላ ፈርጅ ... ሲያዋድዱ ሲያራግቡ መታየታቸው ነው። ጎብራዊቷን ኢትዮጵያ ለማልማት አክራሪነት አይበጅም እንላቸዋለን።

የመደብ-ብሔረሰብ ድርብ ጭቆና ኢትዮጵያ ውስጥ በጎይለሥላሴ ዘመን አልነበረም ማለት ችግሩን አይፈታውም፤ አሁን ችግሩ በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ጠይቆ በጥሞና በመረዳት በሀገሪቱ ውስጥ ያሉት የፖለቲካ ድርጅቶች በሙሉ በጋራ መፍትሔ እንዲሹ ለማድረግ መነሳት ነው። በከፍተኛ ብስለትና ትዕግሥት ተወያይተው የጋራ መፍትሔ እንዲፈልጉ የተጠናከረ ጥረትና ትግል ማድረግ ነው። ሌላው አማራጭ አስከፊ

ሊሆን ስለሚችል ችግሮችን ሰላማዊና ፖለቲካዊ ጎዳና ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። አሁን የትግራይ-ትግሪኝ ጠባብ ብሔርተኞች የፖለቲካ ሥልጣን በኃይል ይዘው አምባገነናዊ ግዛታቸውን አገራችንን ከዳር እስከዳር በሚኑበት ወቅት፥ አክራሪ ብሔርተኞች "በየብሔረሰቡ ተደራጅቶ" ትግሉ ቢቀጥል ልቡ ካበጠውና አእምሮው እየተናደፈ ከመጣው ህወሓት አመራር እምቢተኝነት ከዚያም አልፎ እየጠነከረ በመምጣት ላይ ባለው ሶመታ ጭፍጨፋ ትንኩሳ፥ ቆስቋሽነት፥ አነሳሽነት፥ ገፋፊነት ወደማይመረጠው ዓይነት የትግል ስልት ቢያድግና ቢለወጥ ተከታዩ ሁኔታ አስከፊ ነው። በአመዛኙ ከትግርኛ ተናጋሪው ክፍል ከተመለሱት የህወሓት ጦር አባላት ጋር አያሌ ሌሎች "የብሔረሰብ ድርጅቶችና ሠራዊቶች ውጊያ ሊገጥሙ፥ ጦርነት ሊያካሂዱ ነው" ማለት ነው። ያኔ ታዲያ "የትግራው" ጦር "ከአማራው" ጦር፥ "ከኦሮሞው" ጦር ... ወዘተ ጋር ሲጋጠም በተመሳሳይ ስም የሚጠራው ብሔረሰብ ሕዝብ ደግሞ "የብሔርን ሠራዊት" ደግፍ፥ መግብ፥ እርዳ ሊባል ነው። ያኔ እኮ ነው ታዲያ መመለሻ የማይኖረው፥ ሲታሰብ የሚዘገንን-የወገናችን የርስ በርስ መተላለቅ ሊጀመር የሚችለው ብለን ዛሬ መስጋት፥ መጨነቅና ማሰብም የሚገባን። ኢትዮጵያ ሌላ ሶማሊያ፥ ዩጎዝላቪያ ሩዋንዳ እንዳትሆን መምከርና መጣጠር ያለብን ሁኔታው ከቁጥጥራችን ሳይወጣ ነው። እንደእውነቱ "ሞኝ የሰለቱን ብልኅ ያመቱን" የሚያሰኝ ሁኔታ ዛሬ ያለንበት ዓይነት ነው።

ቀድሞ በፈውዳል ገዥዎቻችን አርቆ አለማየት ሕዝባችንና ሀገራችን በጣም ተጎዱብን። ኋላም ደርግ በኃይል/ወታደራዊ መፍትሔ ፍለጋ ቅድሚያ በመስጠት በተከተለው ጭፍጨፋዎችም ችግሩ ተባብሶ የሀገራችን ፖለቲካ በጠባብ ብሔርተኞች እግር ለሚላቆጥበት ሁኔታ ተዳረግን። እንዲያ ሆኖ አክራሪ ብሔርተኞቹ እንደሚሰበኩት "ሌላውም በየብሔረሰቡ ተደራጅቶ" ጊዜያዊ ኃይልና ሥልጣን ዓይነ-ጎሊናቸውን ያወረባቸውን ጠባብ ብሔርተኞች መሻኮት መጋፈጥ፥ መዋጋት፥ ... ከተጀመረ ኢትዮጵያዊነትን በጉሣ ፖለቲካ እንደጭቃ አቡክተንና በጥብጠን ለፖለቲካ ማጥ ነው የምንዳርጋቸው። ዛሬ "የኢትዮጵያ መንግሥት"፥ "የኢትዮጵያ ጦር ኃይሎች"፥... ለማለት የማይቻልበት፥ ያለው ሠራዊት የትግራይ ትግሪኝ የሆነበት ... ስለዚህም "የመንግሥት ሠራዊት ከዚህ ወይም ከዚያ አካባቢ ሕዝብ ጋር ተጋጨ" ሳይሆን "ትግሪኛ ተናጋሪው የህወሓት ጦር ከአማራው፥ ከኦሮሞው፥ ከነገደ አገው፥ ከአፋር፥ ከሱማሌ፥ ከጉራጌ፥ ከወላይታ፥ ...ወዘተ ሠራዊት" ጋር ነው ሊባል የሚችለው ማለት ነው። ለዚህ ነው በማንኛውም መንገድ ይህ ሁኔታ በሀገራችን እንዳይከሠት መታገል ያለብን።

በዘመነ ደርግ ከተካሔደው የመጨረሻ የሕዝብ ቆጠራ ስንነሳ ያኔ ወደ13 ሚሊዮን ይጠጋ በነበረው የኦሮሞ ብሔረሰብ፥ ያኔ 12 ከፍ ይል በነበረው የአማራው ብሔረሰብ፥ ያኔ ወደ5 ሚሊዮን በሚጠጋው በትግራይ-ትግሪኝ ብሔረሰብ (አሁን በሁለት አገሮች ውስጥ ቢከፍሉትም) ያኔ ከ1 - 3 ሚሊዮን ብዛት በነበረባቸው በሱማሌ፥ በጉራጌ፥ በወላይታ ብ/ሰቦች ሲጠቃለሉ ከ11 ሚሊዮን በማያንሱት በደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦችና በሌሎችም መካከል ነው በወገን ተሰያይተው የሚዋጊበት ሁኔታ የሚፈጠረው ማለት ነው። ከማናቸውም (ጠባቦችም ሆነ አክራሪዎችም) ጋር በ/ሰብ ደረጃ ወግነው ሊዋጉ የማይፈልጉትና የማይሻሉት ክፍሎች ከጠባብና አክራሪ ብሔረተኞችና በቁጥር ቢበዙም ኩተሊየዩ ብሔረሰቦች የጋራ ህይወት የተፈጠሩት ደግሞ ከኢትዮጵያዊነት ውጭ ሌላ ትክክለኛ መታወቂያ ባይኖራቸውም በብሔረሰብ ላይ የተመሠረቱ ጦርነቶች ግን አንዴ ከተጠቃለሉ መሥፈርታቸውም ሆነ ሰለባቸው የተዛባ ስለሚሆን የብ/ሰቦች የርስ በርስ ጦርነት ሲታሰብ እንኳን ይዘገንናል። ከሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች በመወለዱ ብቻ ህፃኑ ልጅ ላይቀር የሚታረድበትን በሺ የሚቆጠሩ የሰው ራሳ በጉርፍ ታጥቦ የሚወሰድበትን ወይም በአውሬ የሚበላበትን፥ የሰው ልጅ እንደዳዋ በገጀራ የሚጨፈጨፍበትን የሩዋንዳውን ሁኔታ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳናመጣው ነው ከልብ መጠበብና አማራጮችን መፈለግ ያለብን።

ከፍ ብዬም እንደገለጥኩት በተለይም አሁን በጣም ተቃቅሮ ባለው ጠባብና አክራሪ ብሔረርተኝነት በተጨመላለቀ የፖለቲካ ሁኔታ ያሉ ችግሮቻችንን ሁሉ በሰላማዊና ፖለቲካዊ መንገድ እንዲፈቱ ባለን አቅም ሁሉ መሞከር አለበት። ሁሉም ነገር ተሞክሮ ሥልጣን ከጨበጡት ጠባብ ብሔርተኞች እምቢተኝነት የተነሳ ባለመሳካቱ ጦርነት ወይም የትጥቅ ትግል ማካሄድ የማይቀር፥ የማይመለጥ አማራጭ ከሆነ ትግሉ መካሄድ ያለበት ከጦርነቱም በኋላ እንዲቆይ ለምንፈልገው የሕዝብ ወንድማማችነትና በረጂም ታሪክ የተጣመረ ሀገራዊ ህላዌው ሲባል፥ በግድ ጎ/ብሔራዊ በሆነ የፖለቲካ ድርጅት አማካኝነት የተለያዩ ብሔረሰብ ተወላጆችን አንድ ላይ በማነሳሳት አስተባብሮም በማታገል መሆን አለበበት። ገዥው ክፍል በአመዛኙ ከአንድ ብሔረሰብ ቢመጣም በአምባገነናዊ ባህሪውና ግብሩ በጠባብ ብሔረተኛነቱ በአመቃው በፀረኢትዮጵያዊነቱ ከብሔረሰቡ ተወላጆችም ጭምር ከፊሉን ያገለለ ነውና በጎብረብሔራዊ ሀገራዊ የተቃዋሚ ኃይል ጥምር ውስጥ እነሱም ሊታቀፉ ይችላሉ: ይገባልም። ሌሎችን ብሔረሰቦች አሰባስቦ በትግፊኛ ተናጋሪው ሕዝብ ላይ ማነሳሳት አሁን ጠባብ ብሔርተኞች በአማርኛ ተናጋሪዎች ላይ (አማራ ባልሆኑ ቋንቋውን ተናጋሪዎች ላይ ጭምር) በአርሲ በሐረርጌና ሌሎችም ሥፍራዎች ሌሎችን አነሳስተው ፈጽመው ካስፈጸሙት ወንጀል የተለየ አይሆንም። አንዱን ወይም ሌላውን ብ/ሰብ በጅምላ እንደጠላት በሚፈርጅ አመለካከትና የዘር ልዩነት ተደራጅተው በሚታገሉ ድርጅቶች እየተመራ የሚካሄድ የትጥቅ ትግል መረን ወደለቀቀ የርስ በርስ ግድያና ጭፍጨፋ የመዝገጥ እድሉ ከፍተኛ ነው። ስለዚህ

ነው የአክራሪ ብሔረተኞች "በየብሔረሰባችን እንደራጅ" የትጥቅ ትግል ፍልሚያ ደረጃ ጎ/ብሔራዊት ኢትዮጵያ ከናካቴው የሚያፈርሳት የሚሆነው:: "እንደተናደደች ሄዳ ቤቷን ሊቃጠሉች" እንዳይሆን - ይቅርብን::

ጎብረ ብሔራዊውና በእኩልነት ላይ ለመተሠረተ አንድነቱና ወንድማማችነቱ ጠንካራ ፍላጐት ያለው ሕዝባችን በከፍተኛ ትዕግሥትና በመቻቻል ጎትቶ ይዞት እንኳን የህወሓትና መሰሎቹ የዘር ፖለቲካ የተወሰኑ ብሔረሰቦችን በጥቃቅን ጉዳዮችና ልዩነቶች ርስ በርስ የማቃረኒያና የማጋጫ ጥረት ... ባለፉት ሦስት ዓመቶች ውስጥ ያደረሰው ጉዳት ቀላል አይደለም:: ለማስታወስ ያህል ጥቂቶችን መጥቀስ እፈልጋለሁ:: አብዛኛዎቹ በተለያዩ ጋዜጣዎችና መጽሔቶች ተዳጋግመው የተጋለጡ ቢሆኑም በአማራውና በአማርኛ ተናጋሪዎች ላይ በአርሲ/አርባጉጉ፥ ...)፥ በሐረርጌ፥ በሰሜን ሸዋ፥ ...ወዘተ የተፈጸሙት የጠባብ ብሔርተኛነትን አስከፊ ገጽታ በትክክል ያሳዩ ናቸው:: በአማርኛ ተናጋሪዎች ላይ እስከዛሬን ተፈጥሮባቸው የማያውቀው "እየተለቀምን እንደከብት ታርደን ልናልቅ ነው" የሚል ሥጋት የፈጠረባቸው በአማራው ውስጥ በጣም ደካማ የአብረው እስከአሁንም ዝቅተኛ የሆነው የብሔርተኛነት ስሜትና ግንዛቤ በመጠኑም ቢሆን እንዲጠናከር በአነሳሾች በትግራይ ትግሪኝ ጠባብ ብሔርተኞችና ጭፍጨፋውን ተግባራዊ ባደረጉት ጥቂት የአሮሞ ጠባብ ብሔርተኞች ላይም ጥላቻና ጥርጣሬ እንዲፈጠርበት አድርገዋል:: ርምጃዎቹ የመላ አማራ ሕዝብ ድርጅት እንዲመሠረትም ምክንያት ሆነዋል:: አማራው ከነገደ አገው ሕዝብ ጋር ተዛንቆና አብሮ የኖረ ሕዝብ ነው:: ከትግራይ ትግሪኝ ሕዝብ ጋር ከሌሎችም ሴማዊ ባህሪያት ካላቸው የኢትዮጵያ ቋንቋ ተናጋሪዎች ጋር (ከትግረ፥ አደርኛ፥ ከሀድኛ ... ተናጋሪዎች) ታሪካዊ ባህላዊ ግንኙነቶች የአብሩትና ያሉት ሕዝብ ነው:: በስፋት በሚኖርባቸው (ጉንደር፥ ሸዋ፥ ጉጃምና ወሎ) ክ/ሀገራት ውስጥ በተለይ ከአሮሞዎች ከአፋሮች፥ ከነገደ አገው፥ ሽናሻዎች፥ ከቤኒ ሻንጉሎች፥ ከትግራይ ትግሪኝ ተወላጆች፥ ከጉራጌዎች፥ ከከንባታና ከሃዲያና እንዲሁም በደቡብ ሸዋ ኗሪ ከሆኑት የሲዳማ ተዛማጅ ብሔረሰቦች ጋር በኢትዮጵያዊነት ተሣስሮ ተግባብቶ በተለያየ ደረጃም ተዋጎዶ የሚኖር ሕዝብ ነው:: የመጠን ጉዳይ እስካልሆነ ድረስ በሌሎችም በምሥራቃዊና በደቡባዊ ክ/ሀገሮች (ሐረርጌ፥ አርሲ፥ ባሌ፥ ሲዳሞ፥ ወለጋ፥ ከፋ፥ ኤሊባቦር፥ጋሙጉፋ) በከተሞች ብቻ ሳይሆን በገጠሮች ጭምር ተሠራጭቶ በአንዳንድ ሥፍራዎች በርከት ብሎ በገጠር ጭምር የሚኖር ሕዝብ ነው:: ከየአካባቢው ተወላጆች ጋርም በብዙ ፖለቲካዊ፥ ማኅበራዊ፥ ኢኮኖሚያዊ፥ ባህላዊ ግንኙነቶች ተሣስሯል:: በትግራይና ኤርትራ ከተሞች ውስጥም በማይናቅ ቁጥር ከሕዝቡ ጋር ተሣስሮና ተግባብቶ ይኖር ነበር::

አሁንም በዘመነ ደርግ የተደረገውን የሕዝበ ቆጠራ ውጤት ስንመለከት በአጠቃላይ በወቅቱ ይኖሩ ከነበሩት የሁሉም ከተሞች ሕዝብ ድምር ውስጥ አማርኛን እንደመጀመሪያው ቃንቋው የሚናገረው ከሳርባ አራት በመቶ በለጥ ያለ ነበር:: ከተሞች ደግሞ በሙሉ ሀገሪቱ የተሠራጨ ናቸው:: አማራው ምናልባትም ከሁሉም ሌሎች ብሔረሰቦች በበለጠ እንድብሔረሰብ በሀገሪቱ ውስጥ በሥፋት ተበታትኖ፥ ተቀላቅሎም ለአያሌ ትውልዶች በኢትዮጵያዊነት ከሌሎች ጋር አየተሣሰረ የኖረና የቀጠለ ሕዝብ ነው:: በአንዳንድ የሃይማኖት ልዩነቶች በሚጠብቁባቸው አካባቢዎች በስተቀር ደግሞ አማራው ከየአካባቢው ተወላጆች ጋር በሥፋት ሲጋባ፥ ሲዋለድና ሲተሣሠር የኖረ ሕዝብ ነው:: እዚህ ላይ ማሳየት የምፈልገው በዚህ መልክ ከቀሩት ብሔረሰቦች ጋር ተደባልቆ በሚኖርበት ታሪካዊ ሂደት ውስጥ አማራው ከሚኖርባቸው ቀደምት ኗሪዎች ጋር በጥቅም አየተሣሠረ ቋንቋና ባህል አየተወራረሰ የጋራ ፍላጎት አየፈጠረ ጥምረቱና ጎብረቱ መሠረት እያገኘ በዚያው መጠንም አየተለመጠ ምምጣቱን ለመግለጥ ነው:: ለዚህም ይመስላል አማራው ከቋንቋና ከብሔረሰብ መለያነት ይልቅ ከሚኖርበት አካባቢ ጋር ራሱን ማዛመድ የሚመርጠውና የሚቀናው ጉጃሜ፥ ጉንደሬ፥ ሸዌ፥ የሐረር/ጌ ልጅ ... ገፋ ሲልም በመኖሪያ አውራጃና ወረዳዎች መጠራት ያዘወትራል:: የአማራውን በኢትዮጵያ ውስጥ በሠፊው መዘራት ያነሳሁት በፊትም ሆነ ዛሬ በአማራው መካከል ጠባብ ብሔርተኛነትን፥ ክለልተኛነትን ወይም አክራሪ ብሔረተኛነትን በአግላይነት መንፈሱ ለማስፈን አዳጋችና አስቸጋሪ የሚያደርጉት ተጨባጭ ምክንያቶች መኖራቸውን ለማሳየትና በተፃራሪ ደግሞ የአብዛኛው አማራ ኢትዮጵያዊነት ስሜትና ጥንካሬም ሰፍኖ እንዲቆይ የሚያደርጉት ከቀሩት ብ/ሰቦች ጋር የተተበተበባቸው ጠንካራ ገመዶች ናቸው:: ይህ ሁኔታና ክስተት ግን በአማራው ላይ ቢቻ የተወሰነ አይደለም::

በጽሁፌ መጀመሪያ ላይ እንደገለጥኩት በርካታዎቹ ብ/ሰቦች በኢትዮጵያ ውስጥ ተበትነውና ርስ በርስም ተደባልቀው ነው የኖሩት:: ለምሳሌ ጥቂቶቹን ላውሳ፤

በተለያዩ መጠሪያዎች የሚታወቁት የነገደ አገው ዝርያዎች በተለይ በ5ቱ የሰሜን ኢትዮጵያ ክ/ሀገሮች ውስጥ ተቢታትነው ተሠራጭተው ከተቀረው ኢትዮጵያዊ ጋር ተቀላቅለው ይኖራሉ:: ኤርትራ ውስጥ ያሉት ብሌኖች በጌምድር ውስጥ ያሉት ቅማንቶች "ቆለኞች" አገው በመባል የሚጠሩት ምናልባትም ቤተእሥራኤሎች (የሃይማኖት ልዩነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ) በትግራይ ውስጥ አገው በመባል የሚታወቁት በጉጃም ውስጥ ጋግሪሣዎችና አገው በመባል የሚታወቁት፥ በወሎ ውስጥ ያው አገው ተብለው የሚጠሩት ... አሁንም በቋንቋ በባህል ርስ በርስ የተሣሠሩ ሆነው በየሚኖሩባቸው አካባቢዎች ከአሉት ሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋርም እንደአማራውና ሌሎቹ ተሳስረው ይኖራሉ::

የነመሓት ጠባብ ብሔረተኞች ይህንኑ የጠባብ ብሔርተኛነት በሽታቸውን በአገደ አገው ውስጥ ለማዛመት ያልሞከሩት ነገር አልነበረም። ኢትዮጵያዊነትን የተላበሰ ግንዛቤውም በዚሁ በኢትዮጵያዊነቱ ላይ የተመሠረተ ሕዝብአንድበመሆኑጠባብ ብሔርተኞች በቀላሉ ሊሸነቃቅት አልቻሉም። ሙከራቸውን አላቋረጡም። በጉጃም አገውዎችን ከሽናሻዎችና ከቤኒሻንጉሉች ጋር አጋጭተዋል።

ነገደ አገው የዛጉዌን ሥርወ መንግሥት ይዞ የነበረ በአፄ ላሊበላ የታነፀውን አኩሪ የታሪክ ቅርሳችንም የሆኑትን ቤተክርስቲያናት ለሀገራችን ያበረከተ ከጥንታዊት ኢትዮጵያ ነዋሪዎች አንዱ የሆነና ለኢትዮጵያ ግንባታ ብዙ ያበረከተ ሕዝብ ነው። ይህ ታሪኩም ኢትዮጵያዊነቱን ያጠነከረለት ሕዝብ ነው።

የኦሮሞው ሕዝብ ወደምዕራባዊውና ሰሜናዊው ኢትዮጵያ ከተስፋፋበት 16ኛው መቶ ዓመት ጀምረው በከፈል ሲዳሞ፣ በከፈል ሸዋ፣ ኢሉባቦር፣ ከፋ፣ ወለጋ፣ ጉጂም፣ ወሎ፣ ሐረርጌ፣ በመሥፈር በየአካባቢው ከሚኖረው ሕዝብ ጋር በሂደት ግንኙነት ትሥሥሩን፣ የቋንቋ የባህል መወራረስን ርስ በርስ መጋባትና መዋለዱን ... ሁለንተናዊ በይነገብሩን እየጠነከረ የመጣ ሕዝብ ነው። በተለይ በሸዋ፣ በወሎ በወለጋ ...የኦሮሞው ሕዝብ ከሌሎቹ በአካባቢው ወይም አዋሳኝ ከሆኑ አካባቢዎች ተወላጆች ጋር በመጋባትና በመዋለድ ጭምር በሥፋት ተሣሥሯል። የትግራይ ትግሪኝ ተወላጆች በተለይም ደግሞ ከትግራይ ክ/ሀገር የሚወለዱት ወደተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች በመሠራጨት በሚሰማማቸው ሥፍራና የሥራ መስክ ተሠማርተው ከአካባቢው ሕዝብም ጋር ተደባልቀው የኖሩና እየኖሩም ያሉ ናቸው። ልክ እንደአማራውና እንደኦሮሞው ከሌሎች ጋር በመጋባት በመዋለድ ቋንቋና ባህል በመወራረስ በጥቅም በሙተሣሠር በኢትዮጵያዊነት ከቀረው ሕዝብ ጋር ተመሣጥሮ ተደጋግፎ የመገንጠል ስሜትን ዓላማን የጉሣ ፖለቲካን ጠባብ ብሔርተኝነትን በሕዝቡ ላይ ለመጫን ያልተቋረጠ ጥረት አድርጓል። እየደረገም ነው። በሁለቱ ጣምራ የትግራይ ትግሪኝ ጠባብ ብሔርተኛና አምባገነናዊ ድርጅቶች ሕዝቡ ከፍተኛና ዕመቃና ጭቆና በከፈሉቹ ውስጥ እየደረሰበት ነው። ሊደለል፣ ሊሸነገል፣ በጥቅም ሊገዛ የሚችለውን ክፍለ ደግሞ በሹመት፣ በሥራ በንግድ ፈቃድ እንዳንዱም በስሜት ብቻ እንዲተባበራቸው እየደረጉት ነው። ይህኛው ክፍል ሠፊ አይደለም። ሠፋ ያለው ክፍል እያዘነ እየተበሳጨ ኢትዮጵያዊነቱን ክብሩንና ሀገሩን ጠባብ ብሔርተኛ "ልጆቹ፣ ወንድሞቹ ..." ሲጎዱበት በአንገል ተግባራቸው ከቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ሲያጋጩትና ሲያጣሉት የማይወደው ለጊዜው ግን በፍርሃት ተውጦና ተዋክቦ ፀጥ ያለ ክፍል ነው።

እንደአሮሞው አማራውና ትግራይ-ትግሪኙ ብሔረሰቦች ብዙት ባይኖረውም በሥፋት ኢትዮጵያ ውስጥ ተሠራጭቶ በመኖሩ በርካታው ክፍል ጉልበቱን በመሸጥ አገልግሎት በመስጠት ላይና እንዲሁም በንግድ ላይ በመሠማራቱ ጥቅሙ ከሚሠራበትና ከኖረበት አካባቢ ጋር ያስተሣሠረው አብሮት ከኖረው ከሌላው ሕዝብ ጋር በጣም እየተያያዘ የመጣው። የኢትዮጵያዊነት ስሜቱም በዚያው መጠን ጠንካራ የሆነው የጉራጌ ብሔረሰብ ነው። በጅግራፊ አቀማመጡ ጠበብ ያለ የደቡብ ሸዋ ክፍል ነዋሪ ቢሆንም በተለያዩ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባኅላዊ ... ምክንያቶች አስገዳጅነት በተለይ በመሐል፣ በምሥራቅ በደቡብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች በሥፋት ተሠራጭቶ ከቀሩት የደቡብ ኢትዮጵያ ተጎራባች ሕዝቦች ጋር በመተባበርም ጭምር ጎብረብሔራዊትዋን ኢትዮጵያ ሀገራዊ ስሜት እያራመደና እያጠናከረ ያለ፣ ለጠባብ ብሔረተኛነትም አላመች ያለሕዝብ ሆኗል።

አሁን በጥቅሉ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ሕዝቦች በመባል የሚታወቁት በርካታ ብሔረሰቦች - ጉራጌ፣ ሃዲያን፣ ወላይታን፣ ሲዳማን፣ ኢያሌ የአሞ ተጎራባች ሕዝቦችን - የም፣ ቡርጂ፣ ከፋ፣ ጋሞ፣ የጌዴዎንን፣ ... ሕዝቦች የሚያካትቱና በበርካታ ህይወታቸው ተዛንቀው፣ ተሣስረው፣ ርስ በርስ ከሚጎራበቷቸው ሌሎች ብሔረሰቦችም ጋር (ኦሮሞ፣ አማራ፣ ሶማሌ ...) በተለያዩ ደረጃ ግንኙነቶችን አጠናክረው የኖሩ ናቸው። ህወሓት/ሻዕቢያ እነዚህ ብሔረሰቦች በየመጠሪያቸው የፖለቲካ ድርጅት ኖሯቸው፣ የብሔረሰባቸው ብቸኛ ተወካዮች የሚሆኑ ክልልተኛ ድርጅቶች በአካባቢው እንዲፈጠሩ ለማድረግ ትልቅ ጥረት አድርገው ነበር። እንደፈለጉት ላይሆን ቀርቶ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ጎብረት ሊፈጠርና የፖለቲካ አቅጣጫውም ጎብረ ብሔራዊነቷ፣ የሕዝቦቿን የጋራ ጥቅምና ፍላጉት በሰኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነትዋ የተጠበቀ ኢትዮጵያን ህላዌ የሚፈልግና የሚደግፍ ሆነዋቸው። በዚህ ሁኔታ የተበሳጩት ህወሓትና መሰሎቹ በየብሔረሰቦች ስም ተለጣፊ ቡድኖችን ፈጥረው ጠባብ ብሔርተኛ ፖሊሲዎች እንዲራምዱላቸው በአካባቢው ለመቀጠል፣ ለማጠናከርር፣ ለመሸም ... ይፋ የሆነ ሥምሪት አደረጉ። ከአሜሪካና ተግባራቸው አልፈው ማስፈራራት፣ ማሠር፣ መግደላቸውን በደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ጎብረት አባል ድርጅቶች ላይ እስካሁንም እንደቀጠለ ነው። የትግራይ ትግሪኝ ቡድን በአማራው ሕዝብ ላይ ብቻ አይደለም የጥቃት በትራቸውን የሠነዘሩት። በአማራው ሕዝብ ላይ የተደረገው ጭፍጨፋና ዕመቃ በሌሎች ላይ ከተካሄደው በመጠኑ የሠፋ፣ በዓይነቱም ይበልጥ ጭካኔ የታየበት ቢሆንም ኢትዮጵያን ገነጣጥሎ የሚያፈራርስ ጠባብ ፖለቲካቸውን አሜን ብሎ ተቀብሎ መሣሪያቸው ወይም ተባባሪያቸው ለመሆን ዝግጁነቱን ገልጦ በተግባር አብሯቸው ያልተሠለፈ ሁሉ የጥላቻ፣ የዕመቃ ዘለፋ በአባላቱ እየዘሩ ማሠር፣ ተጉትቶ ከገባበት የሽግግር ም/ቤት ያለአግባብ መባረር፣ ትንኮሳ ግድያ ጭፍጨፋም ደርሶበታል።

የአፋር ብሔረሰብ አብዛኛው ክፍል በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩት ተወላጆቹ እንደገና በ2 አገሮች እንዲከፈል አይፈልግም። ኢትዮጵያ እንድትገነጣጠልም አይሻም። አንድነቷ በተጠበቀ ኢትዮጵያ ውስጥ- የውስጥ አስተዳደር መብት ተጠብቆለት በእኩልነት አብሮ መኖር የትግሉ ጥያቄ። የአፋር ሕዝብ ፍላጐት ኤርትራን ከገነጠለው የትግራይ ትግሪኝ ጠባብ ብሔርተኞች ዓላማ ጋር አልተጣጣመም። ህወሓት ታዲያ ሥልጣን ከያዘበት ከ1983 ዓም ጀምሮ በ1984 እና 85 ዓም ውስጥ በተለይ ከ05/08/85 ወዲህ በተጠናከረ መልክ የተቀነባበረ ጦርነት ጭፍጨፋ በሻዕቢያና በህወሓት ተካሂዶበታል። የገዋኔው ጭፍጨፋ ከብዙዎቹ አንዱ ነው። አሁንም በአፋር ሕዝብ ላይ ያልተቋረጠ ዕመቃና ጭፍጨፋ እየተካሄደ ነው። የህወሓትና ሻዕቢያ መንግሥቶች ከኢትዮጵያ ሀገራዊ ክልል ውጭ በጅቡቲ ውስጥም በፀረ-አፋር ዕመቃ ላይ ተሠማርተዋል። የታወቀው ሥጋታቸው አፋሮቹ በጅቡቲ ውስጥ ከተጠናከሩ ኢትዮጲያ ውስጥ ላሉት አፋሮች ርዳታና ድጋፍ ሊሰጡ ይችላሉ የሚለው ነው።

ወላይታ ውስጥ ሀረካ በተባለው ሥፍራ የህወሓት ወታደሮች ሰላማዊውን ሕዝብ በማንአለብኝነት በግፍ ጨፍጭፈው፥ የሽግግር ም/ቤት በሚባለው የህወሓት ተቋም ውስጥም ጉዳዩ ተነስቶ እንዲጣራ ተብሎ፥ የመንግሥት ወገንተኛ የሆኑ ሰዎችን በማነጋገር የተቀነባበረ የሐሰት መረጃ ደርድረው በማድበስበስ አጥፊዎች ሳይቀጡ ቀርተዋል። የወላይታ ብሔረሰብ በፊት ያልተጨቆነ፥ ወይም በህወሓት ቋንቋ "ትምክኸተኛ" ሆኖ አየደለም። ህወሓት-ሻዕቢያ ለደቡብ ሕዝብ መመሪያነት በመረጡት ጠባብ ብሔርተኛነት አሜን ብሎ አለመጓዙ ነው።

በሲዳማ ብሔረሰብ ላይ በተደጋጋሚ የህወሓት ጦር ከፍተኛ ወረራና ጭፍጨፋ አካሂዷል። ወደተለያዩ አካባቢዎች በመዝመት በሰው ህይወትና ንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል። በአዋሳና ሌሎችም ከተሞች በረካታ የብሔረሰቡን ተወላጆች አሥሯል። በአቶ ወልደአማኑኤል ዱባለ ላይ የግድያ ሙከራ አድርጐ ነበር። በተለይ ከሲዳማ አርነት ንቅናቄ ጋር ግንኙነት አላቸው ብሎ የሚጠረጥራቸውን አሁንም እያሳደደ ነው። የብሔረሰቡ ወንጀል ለመገንጠልና ለማስገንጠል አብሮ አለመሠለፉና ህወሓት ጠላቶቼ ናቸው በሚላቸው ላይም ለማጥፋት አብሮ አለመሠለፉ ነው። ህወሓት ራሱ ከሚሠነዝረው ጥቃት በተጨማሪ በሰላም የሚኖሩ ተጐራባች ብ/ሰቦችን ርስ በርስ በተለያዩ ጉዳዮች (ራሱ አሁን በፈጠራቸው) ማጋጨት፥ ማዋጋት በባላንጣነት እንዲተያዩ ማድረግ .... ይሁነኝ ብሎ በቋሚነት እየተጠቀመበት ያለ ስልት ነው። መንግሥት ነኝ ካለና ሀገሪቱን በጐሣ ከሸነሸነ ደግሞ ወደ60 ኪሜ ርቀት ላይ የጊዶሎንና የኮንሳን ሕዝብ በወሰን (መሬት) ጥያቄ አበጣብጦ ርስ በርስ እንዲዋጉ አድርጐ "የሁለት ገበሬ ማኅበር በእሣት ተለብልቦ በመቶ የሚቆጠር ሰው ሞቷል፤ በተመሣሣይ ሁኔታ የኮንሶና የዘኤስ ብ/ሰቦች ተዋግተው ከ8 ሰዎች በላይ ሞተዋል"፤ እነደገና በሌላ ወቅት "በወላይታና በጋሞ ብ/ሰቦች መካከልም በተነሣው ግጭት 2 ሰዎች ሞተዋል" እያለ ራሱ ዘግቦታል። ጠባብ ብሔርተኛነትን አነሳስቶ ታዛዥ ቡድኖችን አሠልፎ የርስ በርስ ግጭቶችን አፋፍሞ "በከፋፍለህ ግዛ ስልት እየተጠቀመ ህወሓት ራሱን የሁሉም "የበላይ ጠባቂ፥ አስታራቂ፥ ሰላም ፈጣሪ ቀጭና ተቀጭ ..." ለማድረግ የሚያስችለው ሁኔታ ለመፍጠርም ነው።

የኦሮሞ ሕዝብ አንዱ ክፍል የሆነውን፥ ለፀረ-አንድነት ዓላማውም በቀላሉ ሊያሠልፈው ያልቻለውን የቦረና ሕዝብ ከገሬ ሕዝብ ጋር በሲዳሞ ክ/ሀገር ውስጥ ከማጋጨቱና የቦረናን ሕዝብ በዚህ ተከታታይ ትንኮሳው ለማንበርከክ ከመሞከሩም በላይ ህወሓት የእነዚሁ ሁለት ብሔረሰቦችና ሌሎች ኢትዮጵያውያን ተሰደው ወደሠፈሩባቸው ኬንያ ውስጥ ወደሚገኙ ካምፖችም የርስ በርስ ግጭት እንዲስፋፋ በማድረግ እዚያም አጋድሏቸዋል። ከመጋቢት 26-27/1986 ወንዶገነት ውስጥ በሲዳማና በኦሮሞ ተወላጆች መካከል በህወሓት ደጋፊዎች በተቆሰቆሰ ግጭት ከ5-25 የሚደርሱ ሰዎች መሞታቸው ይታወቃል።

ህወሓት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሙሉ በሙሉ ጠባብ ብሔረተኛነትን መላበስ አለበት፥ መመሪያውም ማድረግ አለበት ብሎ የተነሳ ድርጅት ነው። ጠባብ ብሔርተኛነት ሥር እንዲሰድ ሌት ከቀን እየሠራ ያለ መሠሪና መርዘኛ ድርጅት ነው። የብ/ሰቦች ርስ በርስ መጋጨት፥ ጠባብ ብሔርተኛነትን ያጠናክራል ብሎ ስለሚያምን በተቻለው መጠን ሁሉ የሚናቆሩበትን ሁኔታ ለመፍጠር ይጥራል። የኦሮሞ ጠባብ ብሔርተኞችን በአማሮች፥ በጉራጌዎች፥ በኢሣዎች፥ (ሶማሌዎች) በሐረሪዎችም ላይ አነሳስቷል። ጋምቤላ ውስጥ ኑዌሮችንና አኝዋኮችን አዋግቷል። ጉጃም ውስጥ ቤኒሻጉሎችን ከሽናሻዎች፥፥ ከአርወዎች፥ ከአገውዎች ጋር አጋጭቷል። ዜና አድማስ ቅጽ1፥ ቁ19 በኅዳር 1986 ዓም እትሙ "በነገሌ ቦረና ፖለቲካዊ ውጥረት" በሚል ርእስ እንዲህ ብሎ ጽፎ ነበር፤ -በቦረና/ኦሮሞ ሕዝቦችና በሱማሌዎች መካከል "የዞን ከተማ በሆነችው ኔጌሌና ቦረና ለሁለት ቀናት ውጥረቱ የከፋው በሱማሌዎችና ኦሮሞ በሆኑት ቦረናዎች መካከል ግዛቱ የእኔ ነው በሚል ፍጥጫ በአንድ በኩል የክልል 5 በሌላ ደግሞ የኦሮማያ ባንዲራ ይውለብለብ በማለት እንደሆነ በሥፍራው የተገኙ ምንጮች ገልጠዋል።" ወያኔ ኢትዮጵያን በዘር ካርታ ዘነጣጥሎ አብረው የኖሩትን ሕዝቦቿን በእንዲህ ያሉ ብቃት ባለው አካል ሊወሰኑ በሚችሉ ጉዳዮች ላይም ለማባላት ምን አክለፈለፈው?! ማንስ ወከለው ይህን እንዲያደርግ?! ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀርቶ ከትግራይ ትግሪኝ ብሔረሰብ ሕዝብ እንኳን ምንም ዓይነት ውክልና

ሳይኖረው ነው ከሰሜን እስከደቡብ የጥፋት ዘመቻውን እያስፋፋ ያለው!

በሲዳሞ ክ/ሀገር ውስጥ ህወሓት ስለፈጠረው ሌላ ትርምስ "ጠቢያ" 1ኛ ዓመት ቁ27 ሠኔ 2/86 የሚከተለውን አሥፍሮ ነበር፣ "ለዘመናት ተባብረው በፍቅር የኖሩትን የሲዳማና የተጐራባች ብሔረሰቦች አባላት የጐሣ ፖለቲካ ባመጣው ጣጣ ሰሞኑን ጐራ ለይተው ባካሄዱት ግጭት ለጊዜው ቁጥሩ በውል የማይታወቅ የሰው ህይወት ማለፉንና ከፍተኛ የከብትና የንብረት ዝርፊያ መፈጸሙን ሪፖርተራችን ከሥፍራው በላከልን ዘገባ አመልክቷል::ግጭቱን በተመለከተ የሲዳማ አርነት ንቅናቄ ሠኔ 1 ቀን 1986 ዓም ያወጣውን መግለጫ በመጥቀስ "ወያኔ/ኢሕአዴግ የግዛት ዘመኑን ለማራዘም በሚያደርገው መጠፍጠፍ የሲዳማ ሕዝብ ከአጐራባች ሕዝቦች ጋር እንዲጋጭ ህይወትና ንብረት እንዲጠፉ ብዙ መሞከሩን ..." መግለጫ መጻፉን ጥቅሱን በመቀጠል "የሲዳማ ሕዝብ ከአጐራባች ሕዝብ ጋር መጋጨት ለማንም የማይጠቅም የጠላት ተንኰል መሆኑን ተረድቶና ተገንዝቦ ከአካባቢው ሕዝቦች ጋር አብሮ በሰላም መኖርን እንዲቀጥልበት" ሲል ጥሪ አቅርቧል" ይላል ጠቢያ::

በሲዳሞና ገሙጎፋ ክ/ሀገሮች ውስጥ የሚኖሩት ሕዝቦች ባለፉት 3 ዓመታት ውስጥ እንደታመሱ ነው:: የኖሩት:: የሽግግር መንግሥቱ ራሱ ወታደራዊ አሰሳ አድርጎ "ሽፍቶች" የሚላቸውን መግደሉን፥ መማረኩንና ሌሎችንም ማሠሩን በመገናኛ ብዙኃን ጭምር እየገለጠ ነበር:: እስካሁንም በአንዳንድ አካባቢዎች የህወሓት ጦር ማተራመሱን መግደሉን እንደቀጠለ መሆኑ ይታወቃል:: <u>አእምሮ</u> ጋዜጣ 1ኛ ዓመት ቁ42 (ሠኔ 11 1986) እትሙ እንደሚከተለው ጽፎ ነበር፣ "በደቡብ አሞ ሽለቆዎች አካባቢ በሚገኘው በናኩሌ ወረዳ የጐዲያ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑ ግለሰቦች በአካባቢው ጥሻ መሸጎ በሚገኘው የሽግግር መንግሥቱ ሠራዊት በጥይት መደብደባቸውንና ይህን ዘግናኝ ድርጊት የፈጸሙ የሽግግር መንግሥቱ ሠራዊት አባላት ለፍርድ እንዲቀርቡ ግንቦት 26/86 ዓም በብሔረሰቦች የፖለቲካ መድረክ የአሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ጎብረት አሳወቀ::" ካለ በኋላ በህወሓት ጦር በጐዲያ ቀበሌ ከተገደሉት መካከል ሰባቱን በስም ዘርዝሮ ጠቅሶ ነበር:: በጀንካ ከተማ በዛ ያለ የህወሓት ጦር መሥፈሩንም የአካባቢው ሕዝቦች እንደቋሚ የሥጋት ምንጭ እንደሚያዩት ገልጾ ነበር:: በሆሣዕና ከተማና በሌሎችም የከምባታና ሃዲያ አካባቢዎች የህወሓትን ጠባብ ብሔርተኛ ፖሊሲ የሚቃወሙ ክፍሎች በህወሓትና ተለጣፊዎች አማካኝነት ትልቅ ዕመቃና በደል እየተፈጸመባቸው ነው:: ያለአግባብ ታሥረው የነበሩ የተወሰኑ ሰዎች በማምለጣቸው ህወሓት ከሰዎች ጋር ግንኙነት ሊኖራቸው ይችላል ብሎ የገመታቸውን በማሠርና በመደብደብ ሽብር ለመፍጠር ከመሞከሩም በላይ ለበርካታ ሰዎች ህይወት መጥፋት ምክንያት ሆኗል::

ባለፉት ሦስት ዓመቶች ውስጥ የትግራይ ትግሪኝ ጠባብ ብሔረተኞች በተግባራቸው እንዳረጋገጡት ምንም እንኳ የኢትዮጵያን ሕዝቦች ከፋፍለው ርስ በርስ ለማጋጨት እንዲረዳቸው ስለብሔር ጭቆና መኖርና ስላደረሰባቸውም በደሎች ሕዝቡ ቋቅ እስኪለው ቢቀሰቅሱም በበኩላቸው እነዚያኑ የመደብና ብሔር ጭቆና ሰለባ ሆነው የኖሩትን ሕዝቦች በባሰ ጭቆና ዕመቃ ጭፍጨፋ እሥራት ... እየበደሏቸው ነው . . :: ማንኛውም ጠባብ ብሔርተኛ ቡድን/ድርጅት የራሴ በሚለው ብሔረሰብ ላይ እየደረሰ ነው የሚለውን የብሔር ጭቆና ለማስወገድ እንደተመሠረተ ፓርቲ ወይም መሆኑ ቢታወቅም ጠባብ ብሔርተኛነት ባህሪው፥ ከለልተኛና ፀረዴሞክራሲ በመሆኑ በተለይም እንደኢትዮጵያ ባሉ ጎብረብሔራዊ ሀገሮች በተናጠል የአንዱን ብሔረሰብ ሁኔታና ችግር ነጥሎና ልዩ አድርጐ በማቅረብ የፖለቲካ ችግሮችን ከማወሳሰብ በስተቀር ለመፍታት አያስችልም:: የህወሓት-ሻዕቢያ አገዛዝ በቂ ትምህርትና ተመክሮ እየሰጠን ስለሆነ የጠባብ ብሔርተኛነትን ውሱንነት አስከፊነትና ጎጂነት ሁላችንም በሚገባ እንደተማርን አስፋ አደርጋለሁ:: ርስ በርሱ በተሣሠረ ሕዝብ መካከል ያለውን የተያያዘ ችግር በጋራና በሀገራዊ ደረጃ ነው ለመፍታት የሚቻለው::

በፊውዳላዊ ገዢዎች ለረጂም ጊዜ ተንሰራፍቶ በቆየው ሥርዓት ውስጥ የተለያዩ የጥንካሬ ደረጃዎች የነበሯቸው የመደብና የብሔር ጭቆናዎች እንደበሩ ለማየት የሚያመዛዝን አእምሮና ያልተደፈነ ዓይነ ልቦና እንጂ በአውነቱ የማርክሲዝም ሌኒንዝም ርዕዮተ ዓለምን መቀበልን የሚጠይቅ ጉዳይ በፍጹም አልነበረም:: "መሬተ ላራሹ!" ብሎ የተሠለፈው ወጣት ሁሉ ያኔ ማርክሲስት ርዕዮተዓለምን መመሪያ ያደረገ አልነበረም:: ከአሮጌው ትውልድ ውስጥ 'አፍቃሬ ፊውዳል' የሆነው ክፍል በተለይ አሁን አክራሪ ብሔረተኛነትን በማቀንቀን በትክክል ተገነዘበውም አልተገነዘበው እንደገና ኢትዮጵያን አባሰ ችግር ውስጥ ለመክተት እየተንደረደረ ያለው ክፍል ያኔ የነበረውን ሀቅ እንደታሪክ እውነትነቱ ሊቀበለው ይገባል:: ትውልዱ ያንን የመደብ-ብሔር ጭቆና በበቂ በዚያን ጊዜ ባለመታገሉ ተከታዩ ትውልድ ችግሮችን እንፈታበታለን ብሎ ባመነበት መንገድ ሥርዓቱን አጠናክሮና አምሮ ታግሏል:: የመደብና የብሔር ጭቆናን በአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የጫነ፥ አብዛኛውን የኢትዮጵያ አርሶ አደር መሬት አልባ አድርጐ ለጢሰኝነትና ገባርነት ለምዝበራ የዳረገ ኢፍትኃዊና ኢዴሞክራሲያዊ የሆነ ኋላቀር ሥርዓት

ስለነበር ያ በተራማጅነቱ እየተከሰሰና እየተወቀሰ ያለው ትውልድ ያንን ፊውዳላዊ ሥርዓት ታግሎ በመጣሉ ይኮራበታል እንጂ፥ ይቅርታም አይጠይቅበትም። እንደግለሰብ አቋማቸውን የሚለውጡ እንደድርጅትም የፖለቲካ ፕሮግራማቸውን አመለካከት የሚለውጡ ይኖራሉ። የአንድ ሀገርም፥ የአካባቢም፥ የዓለም ሁኔታዎች ጠንዝተው ስለማይኖሩ ስለሚለዋወጡ ከተጨባጭ ሁኔታ ውጭ ደግሞ መኖርና መሥራትም ስለማይችል አስተሳሰብም አብሮ መለወጡ የሚያስፈልግባቸው ሁኔታዎች በርግጥም ይኖራሉ። ታሪክን፥ ያለፈውን እውነታ ከልሶ መጻፍ ተገቢም ትክክልም አይደለም። ስለዚህ ነው የኢትዮጵያን ታሪክ ጠባብ ብሔርተኞች ወደመቶ ዓመት "እንቶ ፎንቶ"ነት ሊያሳንሱት ሲሞክሩ አክራሪ ብሔርተኞች ደግሞ የነበረን የመደብ ብሔር ጭቆናን በመካድና እንዲያውም አንድ "በማርክሲዝም ሌኒኒዝም የተለከፈ ትውልድ ያመጣው" አድርገው ለማቅረብ ይውተረተራሉ። ሁሉቱም ፍሬ ከርስኪ ናቸው።

ባለፈው አሥር ዓመታት ጊዜ ክልል በዓለም ውስጥ አንድ የአስተሳሰብ ለውጥ መከሠቱ ግልጽ ነው። በተለይ በእኔ አስተያየት ሁለት ተደጋጋፊ ሂደቶች ለዚህ ለውጥ ያበቃው ይመስለኛል። አንደኛው በሶሻሊስት ሥርዓት ውስጥ ለሰው ልጅ የነፃነት የመንፈስና የፖለቲካ ዕምነተ ነፃነት ... መፋፋት ማደግ መጎልበት አስፈላጊ የሆነው የዴሞክራሲያዊ መብት መጥፋት ከሕዝቡ ጭምር ሊደበቅና ሊካድ ካለመቻሉም በላይ ይህን ነፃነት ነፍጉ የቆየው ሶሻሊስት ይባሉ በነበሩት እንደሶቭየት ኅብረት ባሉት አገሮች ውስጥ ሥልጣን የጨበጠው ክፍል ደግሞ ማመቂያ እጆቹ አየዛለበት መምጣቱ ነው። ሁኔታው በድንገት ከተፍ ያለ ሳይሆን የሕዝቡ ነፃነት፥ ዴሞክራሲያዊ መብት ፍላጐትና ጥያቄ ቀስ በቀስ ሲጠናከር ኖሮ ገዥው መደብ ሲመናታና ሲንገዳገድለት ገፍትሮ ለመጣል ምቹ ሁኔታ አገኘ። ጐርባቾቭ ግላስኖስትና ፕሪስቶሪካ በመባል የታወቁትን ዕመቃን ያላሉ ርምጃዎችን ሲወስድ በእነዚህ ስንጥቆች እየሠረገና እየገባ እያሠፋቸውም ግድግዳው እንደተሰበረለት ግድብ የሕዝቡ የታመቁ ጥያቄዎች ጠንክረው ይጐርፉ ጀመረ። በራሱ ላይ ጭምር እምነት እያጣ የመጣው የገዥው ክፍል ሊገታቸው አልቻለም። በምሥራቅ አውሮፓና በሶቭየት ኅብረት ውስጥ የነበረው ሶሻሊስት ኮሚኒስታዊ ... በመባል የሚታወቀው ሥርዓት አወዳደቁ አጓጉል ስለነበረም ጭምር በሥርዓቱ በርዕዮተ ዓለሙ በሀገሮቹም ውስጥ የነበሩትን ጥሩ ነገሮች ከመጥፎዎቹ ለመለየት የማያስችል የተወዛገበ የተመሰቃቀለ የአስተሳሰብ ሁኔታ ውድቀቱን አጅቦ ተንሰራፋ። ይህ እንግዲህ በራሱ በዚያው በሶሻሊስት ሥረዓቱ ውስጥ የነበረው ሂደት ነው። አንደኛው አሁን በዓለም ውስጥ ለተፈጠረው የአስተሳሰብ ለውጥ አስተዋጽዖ ያደረገው ብዬ አምናለሁ።

በሁለቱም ሂደት ደግሞ በዚያው አሥር ዓመት ጊዜ ውስጥ በቀዝቃዛው ጦርነት ተፋላሚ የነበረው ሌላው ጎራ ሰሜን አሜሪካን ምዕራብ አውሮፓን ጃፓንን ... የያዘው ክፍል የተጓዘባቱ ነበር። በአሜሪካ፥ በካናዳ በእንግሊዝና ጀርመን ሥልጣን ላይ የነበሩት ወግ አጥባቂ የቀኝ ፓርቲዎችና መሪዎቻቸው የካፒታሊስቱን ሥርዓት ውስጣዊ ችግሮች አቻችለው በመቀጠል እነዚህ በአመለካከታቸው አክራሪ የቀኝ የሆኑ ክፍሎች የተቆጣጠሯቸው የምዕራብ መንግሥታት የዓለምን ፖለቲካና አኮኖሚ ሁኔታ ስልታማ በሆነና በተቀነባበረ መንገድ ወደሚፈልጉት አቅጣጫ ለመግፋት የቻሉ የዲፕሎማሲያዊ ጨዋታቸውንም ከኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አቅማቸው ጋር አጣምረው ለማስኬድ የቻሉ ስለዚህም በሶሻሊስቱ ጎራ ውስጥ የታዩትን ችግሮች መመናታቶች የሐሳብና የመንፈስ መላላቶች ድክመቶች በሚገባ ሊጠቀሙባቸው የቻሉም ነበሩ። ጎርባቾቭን አይሎ እያባበሉ እያሞካሹ አቀፍ ደገፍ እያደረጉ ... ነበር መመለሻው እስከሚሳነው ያጀቡት። ርስ በርስ ተባብረው እንቅስቃሴያቸውን በአሜሪካ መሪነት አቀናብረው ከፍጥጫ ይልቅ በስልት ተከታታይ ግፊትና ማበረታታትን፥ በመጠቀም ነበር የሶቭየቱን የግዥ መደብ ከአሥረዓቱ በአፍ ጢሙ የደፉት። የሶቭየት ጎብረቱ በአምባገናኖችነት ላይ የተመሠረተ ግዙፍ አማቂ ኃይል ማለትም ዋናው የምሥራቁ ወይም የሶሻሊስቱ ማዕከል መፈራረስ ከጀመረ በኋላ እንዲያውም በውስጣዊ ችግሮች በመዋጡና በማተኮሩ በምሥራቅ አውሮፓ ሀገሮች ላይ የነበረውን ቁጥጥር ሲያላላ በሁሉም አካባቢዎች ይታዩ የነበሩት የሥርዓቱ ንቃቃቶች የማይጠገኑ ሽንትሮች እየሆኑ ስለመጡ የምዕራቡ የገዥው ክፍሎች ደግሞ በአጋጣሚው እየተጠቀሙ የሀገሮችን ውስጣዊ የተቃዋሚ ኃይል እንቅስቃሴዎች በማበረታታትና በማጥፋ ለ60 ዓመቶች ያህል ሲታገላቸው የነበረውን ሥር አት ;ዳድሰው ጣሉት። በእርግጥም በዓለም ልዩ ሁኔታ ተፈጠረ።

የምሥራቁ ወይም የሶሻሊስቱ ክፍል)ክቻይና ከሰሜን

ኮሪያና ከኩባ በስተቀር) በአስከፊ ሁኔታ ውልቅልቁ በመውጣቱ የምዕራብ ወግ አጥባቂ ክፍሎች የካፒታሊስቱ ሥርዓት አፈቀላጤዎች እንዲሁም በለውጡ ግዙፍነትና ስፋት እንዲሁም ፍጥነት የተዋከቡ ክፍሎች በሙሉ እኤአ ከ1987 ዓም ጀምሮ በዓለም በመስፋፋት የበርካታ ፓርቲዎችና የብዙ መንግሥታትም መመሪያ በመሆን ከዓለም ሕዝብ ግማሹ በላይ ይኖርበት በነበረው የሶሻሊስት ክፍልና በምዕራቡም ውስጥ ጭምር ሠፍኖና ተስፋፍቶ የነበረውን አስተሳሰብ፥ አመለካከት፥ ፍልስፍና፥ እምነት ... ለሰው ልጅ የሐሳብ ብልጽግናና እድገት ምንም እንዳላክተ መሳቂያና መሳለቂያ ሊያደርጉት ተነሱ። ዘመቱበትም።

በቻይና በሰሜን ኮሪያና ኩባ ያሉትን ሁኔታዎች ስንመለከት እስካሁን የሌሳውን፥ የካፒታሊስቱን ጎራ የተቀነባበረ ግፊትና ትግል ተቋቁመው ቢቆዩም ለሱቭየት ኅብረትና ሌሎችም የምሥራቅ አውሮፓ ሀገሮች መፈራረስ ውስጣዊ ምክንያቶች የሆኑትን የሕዝቦች የህሊናና የዕምነት ነፃነት ፍላጎት ለዴሞክራሲያዊ ሰብዓዊ መብቶች መከበር ያላቸውን ጥያቄ ማሟላት አልቻሉም። ስለዚህ ወግ አጥባቂ የሆኑት የካፒታሊስቶ አገሮች ገዥ መደቦችና የርዕዮተዓለማዊ አፈቀላጤዎቻቸው የበላይነቱን ይዘው በአቸናፊነት ሶሻሊስተአዊውን አስተሳሰብ ጥንብርኩሱን እያወጡት ነው። አስተሳሰቡ ውስጥ ፍልስፍናውና ሥርዓቱም ውስጥ ለሰው ልጅ ጠቃሚ የሆኑ ቁምነገሮች ግንዛቤዎች ግኝቶች መተክሎች በጥናትና ምርምር ተጨምቀው ተበጥረውና ተ ቅመው መውጣት ለጥቅምም መዋል ሲገባቸው ከእነሱ ጋር የተነካካው ሁሉ በድፍኑ "ውግዝ ከመአርዮስ" እየተባለ ነው። ይህ ሁኔታ ግን የአስተሳሰብ ድህነትን የሚገልጽና ይህንኑ ድህነት የሚያጠነክር ሆያ ሆዬ ነው።

የሶሻሊስቱ አስተሳሰብ ከካፒታሊስቱ ጋር ባደረገው ትግል ስለማኅበራዊ ፍትኅ፥ ዕኩልነት፥ ዓለም አቀፋዊነት፥ ... ወዘተ ከማስተማሩም በላይ መረን የለቀቀ ብዝበዛን፥ የመደብ፥ የብሔር፥ የሃይማኖት የጾታ ጭቆናን፥ ቅኝ ገዥነትን፥ ዘረኛነትን፥ በኋላም የፋሽስቶችን ሥርዓትና ዘረኛ አስተሳሰባቸውን ታግሎ ብዙ ድልም አስመዝግቧል። በተለይ ለሦስተኛው ዓለም በቅኝ ግዛትነት ተይዘው ለነበሩት፥ የዘረኛነት ለለባዎች ሆነው ለነበሩት ሕዝቦች ነፃነት ከፍተኛ አስተዋጽአ አድርጓል። የተመሠረተባቸው መተክሎች ሙሉ በሙሉ መጥፎና ጎጂ፥ የማይሠሩ .... ናቸው ተበለው የሚወረወሩ አይደሉም። ለዓለም ኮፍልስፍና፥ የፖለቲካ ሳይንስ፥ በኢጠቃላይ የአስተሳሰብ ዕድገት ጉልኅ አስተዋጽአ አበርክቷል። አምንታዊና በጐ ገጽታዎች በጥልቅ ተጠንተው ለመደፊቱ የሰው ልጅ ህይወት ጠቀሜታ ያላቸው መተክሎችና መርኅዎች ተገቢ ሥፍራ ሊሰጣቸው ይገባል። ሕፃንን ልጅ ከተጠቀለለበት ጨርቅ (ፎጣ) ጋር አብሮ አይወረውሩም።

ታዲያ ዓለም ውስጥና ባለፉት 10 ዓመታት ውስጥ በደረሰው የአስተሳሰብ ለውጥ፥ ተራማጁና ሶሻሊስቱ ክፍል አምነታዊ ገጽታዎችን እንኳን ለመከላከል ባልቻለበትና በተዋከበበት ሁኔታ አፍቃሬ ፊውዳልና አክራሪ ብሔረተኞችም በተራማጅ ትውልዱ ላይ የሆነ ያልሆኑውን በመለከክ ሊዘምቱ ተነሱ። ምንም እንኳን ዓለም አቀፍ ሁኔታው ለቀኝ አስተሳሰብና አድኃሪ ኃይሎች የተመቻቸ ቢሆንም ኃላቀር አስተሳሰብን ኢሰብዊና ጐጂ የሆነ የፖለቲካ አመለካከትን፥ ... መታገል ተገቢ ነው። አለዚያ ጥሩው፥ ጠቃሚው፥ ትክክለኛው ነገር በተሳሳተ ጐጂ ነገር እየተለወጠ ይቸነፋል። ከአድርባይነት ጋር የተያያዘው መንፈስ ለንቋሳነትን፥ ድንቁርናን፥ የአመለካከት ድኅነትን ያስከትላል። ጊዜ ሰጥቶት ለጉለበተው ለጊዜውም ቢሆን ለአቸንፈው .... ሁሉ ትክክለኛውን ኩተሳሳተው ሳይለዩ ማሸርገድ ያንኑ በወቅቱ የበላይነት የያዘን ሐሳብ እንዳለ እየተቀበሉ ማራገብና ማወደስ ... ዞሮ ዞሮ ሕዝብን፥ ሀገርን፥ ሻገር ሲልም የሰውን ዘርና ዓለምን መጉዳት ሊሆን ይችላል። የሰው ልጅ አእምሮ እጡብ ድንቅ መሣሪያ ነው። በደንብ ኩተሠራበት ፍሬን ከገለባው ለመለየት፥ ለመምረጥ ሮሚያስችል ብቃት ያለው ነው።

የዚያ ትውልድ ተራማጅ ክፍል በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረውን እውነታ ሳይፈራ በመናገሩ፥ በሀገራችን ውስጥ የብሔረሰብና የመደብ ጭቆና አለ በማለቱም አላጠፋም። መፍትሔ በሚፈለግበት ሂደት ውስጥ ያኔ በዓለም ውስጥ በጣም ተስፋፍቶ የነበረውን ተራማጅ አስተሳሰብ እንደተሻለ አማራጭ ለማየት የሚጋብዙት ሁኔታዎች ስለነበሩ ለምን ወደዚያ እንዳዘነበለ ሳይመረምሩ በደፈናው ማውገዝ ትክክል አይሆንም። ትውልዱ ዛሬ ባለው፥ የበላይነት በኃዝው አስተሳሰብ መመዘኛዎች አይደለም ሊገመገም የሚገባው። ስንትና ስንተ የሳይንስ ንድፈ ሐሳቦች ከዓመታት በኋላ በሌሎች ግኝቶች ነው ሲፋለሱ የሚኖሩት። ያውም ዛሬ በአስተሳሰብ ደረጃ ሠፍኖ የሚታየው የሽግግር ወቅት ውዥንብር ነው። ሁኔታዎቹ አልሰከኑም።

የዚያ ትውልድ ድክመትና ስህተት ታዲያ ከሁለቱ ሰፋፊ ጉራዎች አንዱን፥ ካፒታሊስታዊውንና ምዕራቡን ትቶ በሌላው በሶሻሊስታዊውና በምሥራቁ ውስጥ መግባቱ አይመስለኝም። ይህን ለማድረግ ከፍ ብዬ እንደገለጥኩት

ብዙ ምክንያቶች ነበሩትና። በኔ አስተያየት ነገሮች ካለፉ በኋላ ስመለከተው ስህተት የሚመስለኝ፦

ሀ/ በማርክሲዝም ሌኒንዝም ንድፈ ሐሳብ ውስጥ መሠረታዊ ጎፀያች ወይም ጉድለቶች ሊኖሩ ይችላሉ የሚል ጥርጣሬ እንኳን ሳይኖረው እንዳለ ትክክለኛ የሚሠራ ነው ብሎ በመመሪያነት መቀበሉ ከግራው የተወሰነ ክፍል ደግሞ ቀኖናዊ በሆነ መንገድ ያንኑ ንድፈ ሐሳብ ተግባራዊ ለማድረግ መሠማራቱ

ለ/ የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ (ሥርዓቱን፥ የሕዝቦቿን ባህሉትና በመካከላቸው ያለውን ውስብስብና ረጅም ታሪክ ያለው ግንኙነት) በተለይም የገጠሩን ክፍል ሁኔታ በበቂ ሳያጠና በአነስተኛ እውቀትና ግንዛቤ ተመሥርቶ ሊያደራጀው ፥መርቶ ሊያታግለው መነሳሳቱ፤

ሐ ስለብሔረሰብ ጥያቄ አፈታት አስቸጋሪነት ስለጠባብ ብሔርተኛነት አደጋ በቂ ጥናትና ግንዛቤ ሳይኖረው ማርክሳዊ መርሆን በቅንነት ማስተጋባቱ የብሔር ጥያቄን ዴሞክራሲያዊ ገጽታዎችና ይዘት ከጠ/ብሔርተኞች የተደረገበትን ጎሠኛነት፥ ገንጣይነትና ኢዴሞክራሲያዊነት ብወቅቱ ለይቶና አበጥሮ ለማውጣት አለመቻሉ፥ ሁለቱንም ጎጂ ክስተቶች (አክራሪና ጠባብ ገጾች) በቂ ትኩረትና ክብደት ሰጥቶ መታገል ሲገባው አንደኛው ላይ ብቻ ማተኩሩና መረባረቡ

መ በተጨማሪ ልዩነቶችን በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ ሰክኖ በበሰለ ውይይትና ክርክር፥ ተቻቻይ፥ አቀራራቢና አግባቢ አቋሞችንና መፍትሔዎቻቸውን በጋራ ለመፈለግ አለመቻሉ በኔ ግምት የዚያ ትውልድ ዋና ድክመቶቹና ስህቶች ነበሩ። በርግጥ በተለይ ይህን የመጨረሻውን በተመለከተ የሀገራችን ፖለቲካዊ ኋላቀርነት የዴሞክራሲያዊ አሠራር ወግና ልምድ (Tradition) አለመኖር፥ ተዋናይ የነበረው ትውልድ ወጣትና ከእድሜው ጋር የተያያዘ ችኩልነት በስንጣሪም ቢሆን የገባርዕዮተዓለማዊ ቀኖናዊነት ሁኔታውን አክብደውታል። የሶሻሊስቱ ዓለም ፓርቲዎችና መንግሥታት ደግሞ ራሳቸው ተከፋፍለው የየራሳቸውን መስመር የሚደግፉ ቡድኖችንና ድርጅቶች ለማ ፍራት መራኮት ላይ ከመሠማራት አልፈው አጠ ቃላይ በሳልና አጠናካሪ ሀሳብም ሆነ ተግባራዊ ድጋፍ ለመስጠት አለመቻላቸው ገና ተመክሮ ላላካበተ ተራማጅ ክፍል ስህተቶች የመፈጸም አጋጣሚውን አስፍቶበታል። ዛሬ ኢትዮጵያ በጣም አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ነው የምትገኘው። የትግራይ ትግሪኝ ጠባብ ብሔረተኞች ሆን በለው በጎሣ ፖለቲካ በከለልተኛና አምባገነናዊ ክልሎች አገዛዝ በማስፈን ሕዝቡን በበቀል ስሜት በማነሳሳት በማጋጨት በማጣላት ... ጎብረ ብሔራዊዋን ሀገር በማፈራረስ ላይ ናቸው። አክራሪ ብሔረተኞች ለኢትዮጵያ አንድነት ቆመናል ቢሉም ጠባብ ብሔርተኞችን ከብሔረሰቦች፥ ድርጅቶችን ከሕዝቡ ለይቶ በማያስተናገድ የብሔር ጭቆናን መኖር በሚክድ አሠንም የብ/ሰብ ጥያቄን በተመለከተ በመፍትሔ ፍለጋ ላይ በማያተኩር ፖለቲካቸው በጎብረ ብሔራዊትዋ ኢትዮጵያ የወደፊት ጎላዌ በሕዝቦች ጎብረትና ወንድማማችነት ላይ ከጠባብ ብሔርተኞች ያልተናነሰ ጉዳት እያደረሱ ናቸው። ሁለቱም ክፍሎች ከተለያየ አቅጣጫ የኢትዮጵያን ሕዝቦች በእኩልነታቸው የተመሠረተ አንድነት ለመፍጠር ከፍተኛ መስዋዕት ከከፈለው አሠንም ለዚሁ ዓላማ ያለማሳለስ እየታገለ ባለው ዴሞክራሲያዊና ተራማጅ ኃይል ላይ እንደየአቅማቸው እየተረባረቡብት ነው። ጠባብ ብሔረተኞች ይህንን ዴሞክራሲያዊና ተራማጅ ኃይል ለማጥፋት የሚፈልጉበት ምክንያት ግልፅ ነው። እኩልነታቸው የተጠበቀላቸው ዴሞክራሲያዊ መብታ ቸውም የተረጋገጠላቸው የኢትየኝጵያ ሕዝቦች አንድነታቸውን ጠብቀው የሚኖሩባት ጎብረ ብሔራዊት ኢትዮጵያ፥ ለማቆየት የሚችለው ይህ በዓላማው በይዘቱም በግብሩም ጎብረ ብሔራዊና ኢትዮጵያዊ እንዲሁም ዴሞክራሲያዊ የሆነው ኃይል ብቻ መሆኑን አበክረው ስለሚያውቁ ነው። አክራሪ ብሔርተኞች ግን ዋናውን (ከፀረአንደነት ኃይሎች ጋር ያለውን) ቅራኔ ከመለስተኛው የፖለቲካ ዓላማን ከበቀል ስሜት መለየት ባለመቻላቸው ምናልባትም የድሮው ፈውዳሊላዊው ሥርዓት ያንሠራራል የሚል አጉል ተስፋ ... ሊሆን ይችላል። ብቻ ወጣም ወረደ በአንድ ብሔረሰብ ጥያቄ ዙሪያ በብሔረተኛ አስተሳሰብ ላይ ተመሥርቶ በብሔረሰብ ደረጃ ከመደራጀት አኳያ ፀረ-ጎብረ-ብሔራዊነት በሆነ ቅኝት ... ላይ የተመሠረቱት ሁለት ጽንፈኛ አመለካከቶች ጠባብ ብሔርተኛነትና አክራሪ ብሔርተኛነት ሳይዋዋሉ ነገር ግን ተደጋግፈው ጎብረ ብሔራዊትዋን ኢትዮጵያችንን እያጠፉብን ናቸው። በሐሳብ በፖለቲካ በርዕዮተ ዓለም እንታገላቸው። ሁላችንም ኢትዮጵያችንን ከጥፋት ለማዳን ዘብ እንቁም።